ተመስገንና ራቅ ማሠሪያ መንግሥቴ በተባሉ መምህራን አማካይነት በጊዜው ይሰጥ የነበረውን የአማርኛ ትምህርት ማንበብ፣ መጻፍና ቁጥር ተምራለች፡፡ ትዳር ከያዘች በኋላ በአባቴ አስተማሪነት መዝሙረ ዳዊትን ደግማለች፡፡

የወላጆቹ ጋብቻ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፶ ዓመተ ምህረት በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በሥርዓተ ተክሊል ተፈጸመ፡፡ ፶፱ ዓመታት ባስቆጠረው ጋብቻው ፭ ሴቶችና ፯ ወንዶች ልጆች አግኝተዋል፡፡ እንዲሁም ፲፯ የልጅ ልጆች አፍርተዋል፡፡ በጤና እክል ምክንያት ራሳቸውን ካልቻሉ ሁለት ልጆች በስተቀረ ሁሉም በተለያየ የሥራ መስክ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሲሆን ከፊሉ በአገር ውስጥ ቀሪዎችም በተለያዩ የውጪ አገራት ይኖራሉ፡፡

፲፱፻፶ ዓመተ ምህረት በአባቴ ሕይወት ውስጥ ታላላቅ ነገሮች የተፈጸሙበት ዓመት ነው፡፡ ጋብቻ፣ ሥልጣነ ክህነት፣ ሹመትና የድርሰት ሥራውን ማስተም ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ትዳር ከመያዙ በተጨማሪ ሥልጣነ ክህነትን የተቀበለው በዚህ ዓመት ነው፡፡ ይህም የሆነው ጋብቻ ከፈጸመ ከሦስት ወራት በኋላ በሐምሌ ወር ፲፱፻፶ ዓ.ም. ሲሆን ሥልጣነ ክህነትን የሰጡት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ባሰልዮስ ነበሩ፡፡

አባቴ"ሊቀ ጠበብት እያሌው ታምሩ" ተብሎ የተሾመው በዚሁ በ፲፱፻፶ ዓመተ ምህረት ነው፡፡ ሹመቱን የሰጡት ደግሞ የደብረ አሚን ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ የነበሩት አለቃ ፍስሐ ጽዮን ተክለሃይማኖት ናቸው፡፡ የሊቀ ጠበብትነት ማዕረግ ከደብሩ አለቃ ቀጥሎ የሚታይ የምክትልነት ደረጃ ያለው ነበረ፡፡ በዘመናዊና በአብነት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተምሳሌታዊነት ያለው ታላላቅ አገልግሎት የሰጡ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትን ለማክበር የተዘጋጀውን"የመምህራን የመልካም አገልግሎት ሜዳሊያ"ከግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ከተሸለሙ ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ አባቴ ሲሆን ይህም የተፈጸመው በ፲፱፻፶ ዓመተ ምህረት ነው፡፡



# መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና

መጻሕፍት በመድረስ ረገድ ከዐሰራ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ እስከ ዐሰራ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ሦስት ዓመተ ምህረት የነበሩት ሦስት ዓመታት አባቴ ከፍተኛ ሥራ የሠራባቸው ዓመታት ናቸው፡፡ በነዚህ ዓመታት የደረሳቸው መጻሕፍት ሦበት ሲሆኑ እነሱም "መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና"፣ "የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ህግጋት"፣ "የኑሮ መሠረት ለህጻናት"ናቸው፡፡

አባቴ በኢትዮጵያና በቤተ ክርስቲያን ህልውና ዙሪያ ያንዣበበ አደጋ መኖሩን ከተገነዘበበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ዓይነት የማስተማሪያ ዘዴዎችን ቀይሶ ሰርቷል፡፡ ከነዚህ ተግባራቱ ዋነኛው ለእያንዳንዱ ምእመን የሚዳረሱ፥ በኢትዮጵያዊነትና በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ላይ ያተኮሩ መጻሕፍትን ማዘጋጀት ነው፡፡ ሕዝበ ክርስቲያን እንዲማሩበትና ተከራካሪ ሲገጥማቸውም ለመመከት እንዲረዳቸው በማሰብ ትምህርትን በመጻሕፍት ለማዳረስ በጊዜው ማድረግ የሚችለውን ሁሉ አድርጓል፡፡

መጻሕፍትን የማዘጋጀት ሐሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደምን ሊያድርበት እንደቻለ ሲገልጽ፤

"...የቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚዎች እየበዙ፥ ጠበቆች እያነሱ፥ ኑፋቄ እየሰፋ፥ የሃይማኖት ትምህርት እየጠፋ፥ በቤተ ክርስቲያን ቀልጌነት እየተስፋፋ መሄዱን እየተገነዘብኩ ከሄድኩ ወዲህ ...ባልወድ በግድ ባለኝ ዐቅም የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ለመርዳት በመድረክ ላይ ለመስበክና ለማስተማር፥ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ወደሚያደርሰኝ ግዳጅ ውስጥ ገባሁ፡፡" ብሏል፡፡ [44]

ምእመናንን በመጻሕፍት ዝግጅት የማስተማርን ሥራ ስለቸኝ፣ ደከመኝ ሳይል እስከሕይወቱ መጨረሻ ደከሞበታል፡፡ በዚህም የማይመጠን ብዛት

[44] አለቃ አያሌው ታምሩ ፤ ምልጃ እፎይና ሰላም

ያለው ህዝብ እንደተጠቀመበት ይታመናል፡፡ ቤተክህነት ያለጡረታ ከሥራው ባገደችው ዘመን እንኳ ሳይቀር የምእምናንን እርዳታ በማስተባበርና የሕትመቱን ዋጋ እንዲከፍሉ በማድረግ በመጻሕፍት የማስተማር ሥራውን እስከ መጨረሻው ገፍቶበታል፡፡ በዚህ ረገድ ስለነበረው አቋም የሚከተለውን ጽፏል፡፡

"ድኩምኒ ለይበል ጽኑዕ አነ፤ ደካማውም እኔ ብርቱ ነኝ ብሎ ይስለፍ ይላለና ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም ሕይወት በሚደረገው መድኅኒት ፍለጋ ሀይናማው ብቻ ሳይሆን ዕውሩ በመሪ፣ እንካሳው በምርኩዝ ሊሰለፍበት ይገባል ብዬ ስላመንኩ በዚህ የውኅርምብር ዘመን ቤተ ክርስቲያኔ እላውቅሀም ብላ ብታባርረኝም እኔ ግን ቤተ ክርስቲያኔን ለመርዳት እውነተኛውን የሃይማኖት ትምህርት በእግዚአብሔር ቸርነት እየተረዳሁና እያባዛሁ ለምእመናን ኢትዮጵያውያን ወንድሞቼ ለማቅረብ ታጥቄ ተነሥቻለሁ፡፡ እናንተም ታስሬ የማገለግለው አምላክ ለምእመናኖቹ የሚገባውን መናገር፣ በጽሑፍም በቃልም እንደሚገባኝ ለማቅረብ እንድችል ይረዳኝ ዘንድ ቸሩን አምላክ እንድተለምኑልኝ ዐደራ እላችኋለሁ፡፡"[45] በማለት የመምህሩን የሐዋርያውን የቅዱስ ጳውሎስን ፈለግ ተከትሎ፤ ፍጹም ትህትና በተመላበት ሁኔታ ራሱን ይገልጽ ነበረ፡፡

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ከወንጌል እንዲሁም ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንደማይተዋወቁ አድርገው እንደሚስብኩ አዳዲስ ሃይማኖቶች ዋነኛ ዓላማቸው አድርገው ያነጣጠሩት ወጣቱ ትውልድ ላይ ነበር፡፡ እነዚህ ሃይማኖቶች፤ በአንድነት በሦስትነት የሚሠለሱ የሚቀደሱ እግዚአብሔር ዓለም ሥላሴን የሚክዱ፣ ቅድስተ ቅዱሳን እየተባለች የምትወደሰውንና የምትከበረውን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የሚሳደቡ ነበሩ፡፡ አዳዲስ የሃይማኖት ሰለባ የነበረውን ወጣት ትውልድ አስተምሮ ለመመለስ የተለያዩ የማስተማሪያ መንገዶችን ቀይሶ በመሥራት ላይ የነበረው አባቴ፤ የሚነበቡ መጻሕፍት

---

[45] አለቃ አያሌው ታምሩ ፤ መልእክተ መንፈስ ቅዱስ



በማዘጋጀት ረገድ ከ፲፱፻፶፱ ዓ.ም.ጀምሮ እስከ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. ብቻ ሦስት መጻሕፍትን አሳትሟል፡፡

እነሱም "መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና"፣"የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት"፣"የኑሮ መሠረት ለሕጻናት" የሚባሉ ነበሩ፡፡ የ"መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና" ዋነኛ ትኩረት ዶክተር አባ አየለ ተክለ ሃይማኖት የተባሉ ካቶሊካዊ መነኩሴ ለጻፉት የዶክትሬት መመረቂያ መልስ መስጠት ነበር፡፡

በውል በተለየና በታወቀ ምክንያት ከ፬፻፶፩ ዓ.ም. ጀምሮ በግዝት በተለያዩት ሁለቱ የእምነት ጎራዎች መካከል ምንም እንዳልተፈጠረ አስመስለው ለመቀላቀል ለተነሡት ዶክተር አባ አየለ ተክለ ሃይማኖት አባቴ የሰጠው መልስ ከተሰለፈበት ዓላማ ፥ ኃላፊነትና ተልእኮ አንጻር ሲታይ ተገቢነቱ በእጅጉ የጐላ ሆኖ ይታያል፡፡ የዚህ መጽሐፍ አቀራረብ ምንም ዓይነት ማስታመም ያልታከለበት ከመሆኑ ባሻገር በዶክተሩ ድፍረትና ሽፍጥ የተቆጣው አባቴ ስለ እናት ቤተ ክርስቲያን ይሰማው የነበረውን ቅንዓት ቀጥተኛ በሆነና በማያሻማ ቋንቋ የገለጸበት ነው፡፡ በቀደሙ ዓመታት ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ከተስነዘሩት የሃይማኖታዊ ቅኝ ግዛት ወረራዎችና ትንኮሳዎች ሁሉ የከፋ ውጤትን ሊያስከትል እንዲችል ታስቦ ለተሠራው የአባ አየለ መመረቂያ ጽሑፍ አባቴ የሰጠው መልስ በማያዳግም ሁኔታ መርዙን ከነስንኩ ነቅሎ ለመጣል የቻለ ድንቅ ጽሑፍ ነበር፡፡ ይህ መጽሐፍ ባለፉት ሥልሳ ዓመታት እንደ ግንባር ቀደም ማጣቀሻ ጽሑፍ ሲያገለግል ቆይቷል፡፡

"የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂ ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ፡፡" በማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ ፯፥ ፲፭ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ መሠረት በማድረግ ለመጽሐፉ ርዕስ ሰጥቷል፡፡ "መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና" የተባለው የመጽሐፉ ርእስም የማስማሪያ በጎች (መዝ፤ ፻፥ ፫) የተባሉ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያን ምእመናን

ከንጣቂ ተኩላ ጠብቀው ላቆዩአት ቅድስት ሃይማኖታቸው ያላቸውን ጥንቃቄ የሚገልጡበት ቋሚ መፈክራቸው ለመሆን ችሏል፡፡

<u>መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና(፲፱፻፶፫ ዓ.ም.)</u>

"መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና" የተሰኘው መጽሐፍ የተዘጋጀው አባ አየለ የተባሉ ካቶሊካዊ መነኩሴ በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. ለዶክትሬት ዲግሪያቸው ማሟያ ይሆናቸው ዘንድ ለጻፉት መጽሐፍ መልስ ነው፡፡ የዶክተሩ መጽሐፍ ርዕሱ"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ባሕርያዊ አካላዊ ተዋሕዶ የምታምነው ትምህርት" የሚል ነው፡፡

"መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና" የተባለውን መጽሐፍ በጊዜው የነበሩ አበው ሊቃውንት እለቃ ለማ ኃይሉና፣ ሊቀ መዘምራን ተክለ ጊዮርጊስ ጎሹ መርምረውታል፡፡ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ስለ ዝግጅቱ "እኔ ዘክርስቶስ፤ እኔ የክርስቶስ ነኝ" በሚል ንዑስ ርእስ ሥር አባቴ የሰጠው ማብራሪያ እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

"በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው ልዩነት በወር፣ በዓመት ሳይሆን ከዐሥራ ስድስት መቶ ዓመት የበለጠ ዕድሜ ያለው የታወቀና የተጠና መሆኑን፤ ልዩነቱም ክርስቶስ አንድ አካል፤ አንድ ባሕርይ ማለት ብቻ ሳይሆን እኔ የክርስቶስ ነኝ፣ እኔ የጴጥሮስ ነኝ ማለትም ስለ ተጨመረበት፤ ኢትዮጵያ እኔ የክርስቶስ ነኝ ስትል፤ የሮማ ቤተ ክርስቲያን እኔ የጴጥሮስ ነኝ የሚለውን ለራሷ ጎዳና በመከፈቷ፤ የሮም ቤተ ክርስቲያን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዳግማዊ ክርስቶስ ነኝ ከማለቱ የተነሣና ኢትዮጵያ፤ ክርስቶስነትን ከአንዱ ከእግዚአብሔር ልጅ በስተቀር ለሌላው አላውቅለትም ከማለቷ የተነሣ መሆኑን ዓለም በሙሉ ያወቀው ነው፡፡"

"ይህም መለያየት እየጨመረ ሄዶ ሄዶ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያን ሁሉ እኔ የክርስቶስ ነኝ ማለትን እኔ የጴጥሮስ ነኝ በማለት እንዲለወጡ፤ እንዲሁም የሮም ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት በአንድ በኩል የክርስቶስ ባሪያ የጴጥሮስ ተከታይ ነው የሚለው ስም ለበሰ ወሬ እያስተያየች በአንድ በኩል የሮም ሊቃነ ጳጳሳት ዳግማዊ ክርስቶስ



መሆኑን እንዲያውቁ፤ ከዚህም ሌላ ማንኛውም ክርስቲያናዊ ወንጌልን ምክንያት አድርጎ ከባዕድ አገዛዝ ቀንበር ሥር እንዲውል፤ እሺ ያላትን በስብከት፤ እንቢ ያላትን በሰለት እያስፈራራች በአደረገችው ትግል እንደ በግ በተኩላ መካከል ከተላኩት ኢትዮጵያውያን አንድ እንኳን የተመለሰ የለም፡፡ ይህንንም እኔ ከማውቀው ተናገርኩ እንጂ ዓለም የሚያውቀው ታሪክ ነው፡፡"

<u>የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት (፲፱፻፶፫ ዓ.ም.)</u>

"የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት" በተሰኘው መጽሐፍ መቅድም ውስጥ የሚከተለው መግለጫ ሰፍሯል፡፡"... በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ፡፡ አሜን፡፡ አብን ወላዲ ወልድን ተወላዲ መንፈስ ቅዱስን ሠራጺ ብዬ ልዩ ሦስት አንድ አምላክ በሚኾን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኜ ረድኤቱን አጋዥ አድርጌ በሕገ ልቡና፣ በሕገ ኦሪትና በሕገ ወንጌል እየተሻሻለ እያደገ የሄደውን የኢትዮጵያን መሠረታዊና መንፈሳዊ ታሪክ ለመጻፍ ይህን መቅድም አዘጋጀሁ፡፡..."

የዚህ መጽሐፍ ዋነኛ ዓላማ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውን ከጥንት ፍጥረት ጀምሮ እንዴት በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንተው እንደ ኖሩ የሚያስተምር ነው፡፡ አባቴ መጽሐፉን ስማሳተም የገንዘብ ዐቅም አልነበረውም፡፡ ይህ መጽሐፍ ከግርማዊ ጃንሆይ በተሰጠ ድጋፍ ለኅትመት ሊበቃ መቻሉ በመግቢያው ላይ የተገለጠ ሲሆን መጽሐፉ ያተኮረባቸው ጉዳዮች በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

አባቴ በመጽሐፉ ዝግጅት ውስጥ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውን ቅርሶችና ውርሶች ናቸው ብሎ የሚያስተዋውቃቸውን ታሪካዊ ሁነቶች እውነትነት የሚያስመሰክረው በመጽሐፍ ቅዱስ ዋቢነት ነው፡፡

በዚህ መጽሐፍ ከሚያነሣቸው ጉዳዮች አንዱ ንግሥተ ሳባ አምልኮተ እግዚአብሔርን የተማረችው ከንጉሥ ሰሎሞን ነው የሚሉ ክፍሎችን የሚሞግትበት ነጥብ ነው፡፡ የንግሥተ ሳባን ታሪክ እንደ አፈ ታሪክ የሚቆጥሩትም ሆነ የኢትዮጵያ ንግሥት አልነበረችም የሚሉት ሙግር

ንግሥተ ሳባ አምልኮተ እግዚአብሔርን ከንጉሥ ሰሎሞን እንደ ተማረች አድርገው በማቅረባቸው ይመሳሰላሉ፡፡ አባቴ ግን መጽሐፍ ቅዱስን እማኝ አድርጎ ንግሥተ ሳባ ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ከመሄዱ በፊት እግዚአብሔርን ታመልክ እንደ ነበረ በማስረገጥ ይሞግታቸዋል፡፡ ለዚህም እማኝ አድርጎ የሚጠቅሰው ንግሥቲቱ ገና ከአገሯ ለትነሣ ለምን ጉዳይ ወደ እርሱ እንደ ሄደች መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር "የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ወደ እርሱ ዘንድ መጣች" መጽ.ነገ.ቀዳ.ምዕራፍ፲፥ ፩። ከማለት ውጪ ሃይማኖት ከእርሱ ልትማር መጣች አይልም፡፡

በተጨማሪም በተመሳሳይ ምዕራፍ ቁጥር ፱ ላይ "አንተን የወደደ በእስራኤልም ዙፋን ላይ ያስቀመጠህ አምላክ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን" ያለችውን በመጥቀስ ይህ አባባል ጥንቱንም ለአምልኮተ እግዚአብሔር እዲስ እንዳልነበረች ከሚያሳይ ውጪ አዲስ ተማሪ የሚናገረው አባባል እይደለም በማለት ይሞግታል፡፡ ይህንኑ ለማጽናትም በማቴዎስ ወንጌልምዕራፍ ፲፪፥፵፪ "ንግሥተ አዜብ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፈርድበታለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና እነሆም ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ፡፡" ሲልጌታ የተናገረውን በተጨማሪ ማረጋገጫ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያቀርባል፡፡ወጣት ኢትዮጵያውያን ወገኖቹን ለማትጋትና ለማንቃት በማሰብ ይህ መጽሐፍ እንደ "መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና" ሁሉ የተመሰገነና ተጠቃሽ ሊሆንለት የቻለ መጽሐፍ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

## የኑሮ መሠረት ለሕፃናት (፲፱፻፵፫ ዓ.ም.)

ሕፃናት ከልጅነት ዕድሜያቸው ጀምሮ ማንነታቸውንና እምነታቸውን ጠንቅቀው እንዲያውቁ የሚረዳቸው መጻሕፍት ሊዘጋጅላቸው እንደሚገባ የአባቴ እምነት ነበረ፡፡ በመሆኑም "ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም" ምሳሌ ፳፪፥ ፮። የሚለውን መሠረት በማድረግ ለሕፃናት የሚሆን መጽሐፍ አዘጋጅቷል፡፡ ርእሱም «የኑሮ መሠረት ለሕፃናት» የተሰኘ ነው፡፡



ይህ መጽሐፍ የታተመበት ዘመን ሲላው ቀርቶ በዘመናዊ ትምህርት ቤቶችም እንኳ ለሀጻናት የሚሆን የመጻሕፍት ዝግጅት ትኩረት ያላገኘበት ጊዜ ነበር፡፡ አባቴ መጽሐፉ በተዘጋጀበት ዘመን የነበረውን ማኅበራዊ፥ ምጣኔ ሀብታዊና ሥነ መንግሥታዊ ምስቅልቅልና በተተኪው ትውልድ ላይ ሲመጣ የሚችለውን ፈተናም ለመገመት የቸገረው አይመስልም፡፡ ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ከ፶ ዓመታት በፊት ቢሆንምዘመን አይሽሬ ከመሆኑ የተነሳ ዛሬ ላይ ያለውን ትውልድ እያየ የጻፈው የሚመስል ይዘትም አለው፡፡ይህን በተመለከተ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ካሰፈረው ውስጥ የሚከተለው ይገኛል፡፡ "...ይህን መጽሐፍ ላዘጋጅ ያሰብኩበት ምክንያት የሚከተለው ነው፡፡ በዚህ በአዲሱ ዘመናችን ወላጆች ልጆቻቸውን ከተማሪ ቤት አስገብተናል፤ ልጆችም ከተማሪ ቤት እንውላለን የሚለውን ቃል ምክንያት በማድረግ ወላጆች ልጆቻቸውን የማይሠሩ የማይቀጡ፤ ልጆችም ወላጆቻችን ይቆጡናል ብለው የማይሰሩና የማይደነግጡ ከመሆናቸው የተነሣ የአስተዳደግና አስተዳደር ሥነ ሥርዓት ፈርሶ፤ የኑሮ መሠረት ተደምስሶ ይታያል፡፡ ..."ይላል፡፡ መጽሐፉ እንደ ስሙ ሁሉ ለኑሮ መሠረትነት የሚያስፈልጉ ምክሮችን ያካተተ ነው፡፡

# ሹመት - ሺ ሞት

አባቴ በሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢነቱና በደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጠበብትነቱ የሚጠበቅበትን የሥራ ኃላፊነት ከመወጣት ባሻገር ሙሉ ጊዜውን ለቤተ ክርስቲያንና ለአገር አገልግሎት በመስጠቱ በርከት ባሉ የቤተ ክርስቲያንና ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ጉዳዮች ሁሉ ላይ አስተዋጽኦው እጅግ እየጐላ መጣ፡፡

የተጠራበትን ሐዋርያዊ ተልእኮ ለማሳካትም ያለምንም ገደብ በሙሉ ኃይሉና ጉልበቱ ይሠራ ነበረ፡፡ በዚህ ምክንያት ቀደም ብሎ ገና በወጣትነቱ የጀመረውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ሥርዓትና ብሔራዊ አስተዋጽኦ ለትውልዱ ማስተማርና ኢትዮጵያውያን ምንነታቸውንና ማንነታቸውን አጥብቀው እንዲይዙ የመምከር ጥረቱን አጠንክሮ እየሠራበት ነበረ፡፡

የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጠበብት በነበረበት ዘመን ወጣቶችን ለማደራጀትና የአገራቸውንና የቤተክርስቲያናቸውን የራሳቸውንም ማንነት ጠንቅቀው እንዲያውቁ ለማድረግ ባደረገው ከፍተኛ ጥረት በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ግምባር ቀደምና አንጋፋ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንዱ የሆነውን "ምክሐ ደናግል" የወጣቶች የሰንበት ትምህርት ቤት አቋቁሟል፡፡የመሰብሰቢያ አዳራሽ ለማሠራት የሚያስችለውን የገንዘብ ዕርዳታ እንዲያገኙ የገቢ ማስገኛ በዓል ሐሳብ በማመንጨት፣በበዓሉ ላይ ወጣቶቹ የሚያቀርቡትን መንፈሳዊ ተውኔት በመደፍ፣ በበዓሉ ላይም ተጽዕኖ ማሳደር የሚችሉ የክብር እንግዶችን በመጋበዝ ከፍተኛ ድጋፍ አድርጓል፡፡

በጊዜው የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ የነበሩት የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እንደራሴና የሐረር ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስና ከፍተኛ የቤተ ክህነትን ሹማምንት በክብር እንግድነት ተገኝተው ለማኅበሩ መጠናከር ያላቸውን የሐሳብና የገንዘብ ዕርዳታ እንዲሰጡ ሁኔታዎችን



አመቻችቷል፡፡ በዚህ ዝግጅት ላይ የክብር እንግዳ ሆነው የተገኙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከፍተኛ የገንዘብና የሐሳብ ድጋፍ በማድረግ ኅብረተሰቡ ወጣቶቹን እንዲደግፋቸው ባቀረቡት ጥሪ ምክንያት ትልቅ መነቃቃት በመፈጠሩ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመጀመሪያው የማኅበሩ መሰብሰቢያ አዳራሽና ጽሕፈት ቤት ሊገነባ ችሏል፡፡ ማኅበሩ የተቋቋመው የካቲት ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ.ም. ሲሆን እስከ ዛሬ የሚጠራበትን ምክሐ ደናግል[46] የተሰኘውን የማኅበሩን ስም ያወጣው አባቴ ነው፡፡

"አለቃ" የሚለው ማዕረግ ለአባቴ የተሰጠው በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት አስተዳዳሪ ሆኖ በተሾመ ጊዜ ነው፡፡ አለቃ ፍስሐ ጽዮን ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ለደብሩ አስተዳዳሪ እስኪመደብ ድረስ ለጊዜው በተጠባባቂነት የአስተዳደሩን ሥራ እንዲመራ ኃላፊነት ተሰጠው፡፡ የተሰጠውን ኃላፊነት የሚገልጥ ደብዳቤ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባሰልዮስ እንደራሴ ከነበሩት ከአቡነ ቴዎፍሎስ ተፈርሞ ሲመጣ እልቅናው ለሱ አይገባም የሚሉ ወገኖች ተቃውሞ ፈጠሩ፡፡

ተቃውሞው ወደ አድማ በመቀየሩ አባቴ ወደ ቅጽረ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገባ ለማገድ ሙከራ አደረጉ፡፡ የረብሻው አፍአዊ ምክንያት ዓይኑ ስዉር አይሾምብንም የሚል ቢሆንም ውስጥ ለውስጥ ይንቀሳቀስ የነበረው ምክንያት ግን ለአንድ ቤተሰብ የማድላትና ሹመትን እንደ ውርስ የመጠየቅ ዓይነት አዝማሚያ የነበረው ነው፡፡ ጉዳዩ ይኸ ሆኖ ሳለ የፓትሪያርኩ እንደራሴ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስና አባቴ ከአንድ የትውልድ አካባቢ የመጡ በመሆናቸው በወገናዊነት እንደተፈጸመ በማስመሰል ክሳቸውን ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ አቀረቡ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አባቴ ከሃያ ዓመታት ላላነሰ ጊዜ በነጻ አለምንም ክፍያ ለደብሩና ለአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ያደረገውን ከፍተኛ ሐዋርያዊ አገልግሎት የሚያውቁ የተክለ ሃይማኖትና አካባቢው ምእመናን በተለይም ተደማጭነት የነበራቸው የአካባቢው ሽማግሌዎች ባደረጉት

46 "ምክሐ ደናግል" ከግእዝ ወደ አማርኛ ሲመለስ "የደናግል መመኪያ" ማለት ሲሆን የደናግል መመኪያ ለሆነች ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መታሰቢያነት የተደረገ ነው፡፡

ጥረት ጉዳዩ ለንጉሠ ነገሥቱ ለአፄ ኃይለ ሥላሴ ዳኝነት እንዲቀርብ ተደረገ፡፡

ተቃዋሚዎቹ ብዙ ለመምሰል በማሰብ የተቃውሞው ውስጥ ምስጢር ያልገባቸውን ሰዎች ጭምር በማሳሳት ተሰባስበው ቀረቡ፡፡ ካህን ለመምሰል ራሳቸው ላይ የካህናት ሻሽ ጠምጥመው ነበረ፡፡ ከንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን ፊት ሲቀርቡ አባቴ ከመረጡ በቀር ሌላ ሰው አብሮት አልነበረም፡፡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ፣ የግርማዊነታቸው የዕልፍኝ አስከልካይ ሜ/ጀነራል አሰፋ ደምሴና ጥቂት ባለሥልጣኖች እንዲሁም ከተክለ ሃይማኖት አካባቢ የመጡ ታዛቢ ሽማግሌዎች የነበሩ ሲሆን የክብር ዘበኛ ወታደሮችም ቦታ ቦታቸውን ይዘው ቆመው ነበረ፡፡

ተቃዋሚዎቹም " እኛ እያለን አቡነ ቴዎፍሎስ በአገር ልጅነት የማይገባውን ሰው ሾሙብን" የሚል ክስ አቀረቡ፡፡ በጉዳዩ ላይ አቡነ ቴዎፍሎስ መልስ እንዲሰጡ ግርማዊ ጃንሆይ ሲጠየቋቸው "ሊቀ ጠበብት" ብለው የሾሙት የቀድሞው የደብሩ አለቃ መሆናቸውን በመግለጥ ይኸውም የተደረገው ቅዱስ ፓትሪያርክ አቡነ ባስልዮስ ተጠባባቂ ሹም እንዲሆን በሰጡት ትዕዛዝ መሠረት መሆኑንና እሳቸውም ይህንኑ ተመርኩዘው አለቃ እስኪሾም ደብሩን እንዲጠብቅ ማዘዛቸውን አስረዱ፡፡

የቅዱስነታቸውን መልስ ካዳመጡ በኋላ ግርማዊነታቸው በአንድ ወገን ተሰብስበው ወደቆሙት ተቃዋሚዎች እየተመለከቱ "በምን ምክንያት ነው አይሾምብንም ያላችሁት?"ብለው ጠየቁ፡፡ አንድ ሰው እየተቻኮለ መልስ ሰጠ፡"ግርማዊ ሆይ! ፍትሐ ነገሥት ዓይነ ሥዉር እንዳይሾም የከለክላል፡፡" አላቸው፡፡

እርሳቸውም "በየትኛው አንቀጽ ላይ?" በማለት መልሰው ጠየቁ፡፡

"ግርማዊ ሆይ! በየትኛው አንቀጽ ላይ እንደሆነ አላውቅም ነገርግን እንደ ሕጉ ብርና ወርቅ አይለይምና ሊሾም አይገባውም፡፡" አላቸው፡፡



"ገበዙ የት ሄዶ ነው እሱ ብርና ወርቅ የሚቆጥረው? ከ ፳ ዓመት በላይ ሲያስተምራችሁ ያላያችሁትን የዓይኑን መጥፋት እንዴት አሁን አያችሁት?ያልተማረው የተማረውን እንዲህ ሲዘልፈው ማየት ያሳዝናል!"

በማለት የቁጣ ቃና ባለበት ድምጽ ተናገሩ፡፡ ወደ አቡነ ቴዎፍሎስ እያዩ "አባታችን ለመሆኑ ለእርሱ የሚመጥን የማዕረግ መጠሪያ አጥተው ነው? እኛ አለቃ ብለነዋል ፡፡ " በማለት "አለቃ" እየተባለ የሚጠራበትን የማዕረግ ሥም ከነሹመቱ ሰጡት፡፡በማስከተልም "ሾመነዋል አንሽረውም፡፡" ብለው ተናገሩ፡፡ አባቴን ደግሞ "አንተም ቂም አትያዝባቸው፡፡ አስተምራቸው፡፡" አሉት፡፡

ከዚህ በኋላ በቦታው የነበሩ ወታደሮች ተቃዋሚዎቹንና አጃቢዎቻቸውን እያቻኮሉ አስወጧቸው፡፡ አባቴም ንጉሠ ነገሥቱ በሰጡት ፍርድ የተሰማውን ደስታ ከገለጠ በኋላ "ሕዝብን በእኩልነት በማየት በሰጠኸው ፍርድ የተነሳ የጠፋው ዓይኔ በኃይለ ሥላሴ ብርሃን አየ" የሚል መንፈስ ያለው ቅኔ ተቀኘላቸው፡፡

አባቴ የደብረ አሚን ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አለቃ ሆኖ መሾሙ ይፋ በሆነበት ብዙ ሕዝብ ተገኝቶ ነበረ፡፡ በዚህ ሥነ ሥርዓት ላይ"ለሃያ ዓመታት ጉባኤውን በዚህ አውደ ምሕረት ላይ ሳስተምር ነጻና ደስተኛ ነበርኩኝ፡፡ አሁን በአምላክ ፈቃድ ሹመቱ በግድ መጣብኝ፡፡ ሹመት ማለት ለእኔ ሺ ጊዜ ሞት ማለት በመሆኑ አልተደሰትኩም፡፡ ሆኖም የቤተክርስቲያኑ ጠባቂዎች እኔ ብቻ ሳልሆን በይበልጥ እናንተ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት አባቶችና ምዕመናን ሁሉ ስለሆናችሁ ሁላችሁም ቤተክርስቲያኑን እንድትጠብቁ በእግዚአብሔር ስም አደራ እላችኋለሁ፡፡" በማለት ንግግር አደረገ፡፡

ከ ፲፱፻፷ ዓ.ም. እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. ድረስ በዘለቀው የስድስት ዓመታት የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪነት የሹመት ዘመኑ አባቴ ከሠራቸው ሥራዎች ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

፭ኛ/ ታህሣሥ ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ.ም. ጃንሆይ የጻድቁን የአቡነ ተክለሃይማኖትን ዓመታዊ ክብረ በዓል ለማክበር በደብሩ በተገኙበት ሰዓት ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ ስላሳየው የአስተዳደር ብቃት ካመሰገኑት በኋላ ምን እንዲደረግለት እንደሚፈልግ ሲጠይቁት ለራሱ ምንም የሚፈልገው ነገር እንደሌለና ይልቁንም የደብሩ ካህናት እንደሌሎች ታላላቅ አድባራትና ገዳማት ቋሚ ገቢ የሚያገኙበት የገቢ ምንጭ እንዲፈቀድላቸው አመልክቷል፡፡በዚህም ቋሚ የደመወዝ በጀት ድጋፍ አስገኝቷል፡፡ ለእርሱ የሚሆን ድጋፍ ለማድረግ አስበው ሲጠይቁት የካህናቱ ይቅደም በማለቱ የተደሰቱት ንጉሠ ነገሥት ቆየት ብለው ባደረጉት ክትትል በኪራይ ቤት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ እንደሚኖር ስላወቁ በአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በኩል ለተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ቅርበት ያለው የመንግሥት ቦታ ተፈልጎ እንዲሰጠው በማዘዛቸው እስከ ህይወቱ ፍጻሜ የኖረበትን መኖሪያ ቤት ለመሥራት ችሏል፡፡

በወታደራዊው መንግሥት ዘመን ከተሾሙ አስተዳዳሪዎች መካከል ሁለት አስተዳዳሪዎች "ጃንሆይ ቦታ ይሰጥ ያሉት ለደብሩ አስተዳዳሪ መኖሪያ ቤት መሥሪያ ነው እንጂ ለእሱ በግሉ ሊኖርበት አይደለም"የሚል ምክንያት በመስጠት አባቴን ከቤቱ ለማስወጣት ብዙ ያልተሳካ ሙከራ ያደረጉ ሲሆን ጉዳዩን በጥልቀት ለማያውቁ የህብረተሰቡ ክፍሎችም ይህንኑ ህሰተኛ መረጃ አሰራጭተዋል፡፡ ይህ የቤት ሥራ ጉዳይ ገና ከጅምሩ ሲወጠን ቦታውን የፈቀደው ማዘጋጃ ቤት በሰጠው ካርታ ላይ የወቅቱ የከተማዪቱ ከንቲባ ክቡር ዶክተር ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህ የፈረሙበት ሲሆን በግልጽ እንደሚታየው"ለእለቃ አያሌው ታምሩ መኖሪያ ቤት መሥሪያ"ተብሎ የተመዘገበ ነበረ፡፡

፮ኛ/ በተክለሃይማኖት አካባቢ ይገኙ የነበሩ ዓይነ ሥውራን እንዲሰባሰቡ በማድረግ ከሙዳየ ምጽዋት ገቢ የተወሰነ ወጪ ተመድቦላቸው ትምህርት ከተማሩ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀጥረው እንዲያገለግሉ በማድረግ ከልመና ኑሮ እንዲላቀቁ ለማድረግ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ሞክሯል፡፡ ይህንን በተመለከተ አቶ ጥበቡ ሙላት

የተባሉ ዓይነ ስዉር የአካባቢው ኗሪ ከዚህ የሚከተለውን የጽሁፍ ምስክርነት ሰጥተዋል፡፡ "እባታችን እሰቃ አያሌው ታምሩ የደብረ እሚን ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሳሉ ዓይነ ሰዉራንን ከልመና እየነጠሉ ሙዳየ ምጽዋት እየሰጡ በትምህርት በኩል ኋላ ቀር የሆኑትን ትምህርታቸውን እንዲያዳብሩ እያደረጉ እሁን ዓይነ ሰዉራኑ ፰ መቶና ፱መቶ ብር እየበሉ ይገኛሉ፡፡ እኔንም ይህንን ደብዳቤ የጻፍኩትን ከልመና ተገላግዬ ቤተ ክርስቲያንን እንዳገለግል እሳቸውም ሆኑ በሰው አስጠይቀውኛል፡፡ ዕድሌ ሆኖ ግን በምክራቸው አልተጠቀምኩበትም፡፡ "በማለት ስለሁኔታው የሚያውቁትን በጽሁፍ ገልጠዋል፡፡

፫ኛ/ የአካባቢውን ሕዝበ ክርስቲያን በማስተባበር የቤተ ክርስቲያኑ ምድረ ግቢ በአግባቡ ተስተካክሎ በአስፓልት ንጣፍ እንዲሠራና በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ምእመናን የሚጠለሉባቸው ታዛዎች እንዲኖሩት አድርጓል፡፡

፬ኛ/ ደብሩን የሚያገለግሉ እየመሰሉ የደብሩ የገቢ ምንጭ የነበሩ የከተማና የገጠር ቦታዎችን በእጇ መናኛ ወስደው የነበሩ ሰዎች እንዲመልሱ አድርጓል፡፡

፭ኛ/ ሊቀ ጠበብት ሳለ ያቋቋመው "ምክሐ ደናግል" የወጣቶች የሰንበት ትምህርት ቤት በተጠናከረ መንገድ እንዲደራጅና በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች እየታገዘ ወጣቶችን እንዲያሰባስብ አመራር በመስጠት እንዲሁም ያላሠለሠ ክትትል በማድረግ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡

፮ኛ/ ምእመናን የሚደራጁበትንና በተቀናጀ መንገድ የኢጥቢያ እብያተ ክርስቲያኖቻቸውን ከማንኛውም ዓይነት ተጽእኖ ነጻ አድርገው በራሳቸው ባለቤትነት እንዲያስተዳድሯቸው ሥልጣን የሚሰጣቸውን የሰበካ ጉባዔ ተግባራዊ በማድረግ ረገድም ለተፈጻሚነቱ እርሱ አስተዳዳሪ በነበረበት በደብረ እሚን ተክለሃይሚኖት ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያውን የሰበካ ጉባዔ የመመሥረትና የማቋቋም ተግባርን ፈጽሟል፡፡

፯ኛ/ በተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ምክንያት ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን ከሚወስዱት የተለያየ የምግብና የመጠጥ ዓይነት የአለቃው ድርሻ ነው እየተባለ ወደ መኖሪያ ቤታችን ይመጣ የነበረውን ምግብና መጠጥ እኔ የምተዳደርበት ገቢ ያለኝ ሰው ነኝ በማለት ረዳት ለሌላቸው ሰዎች እንዲሰጥና ወደቤት እንዳይመጣ አድርጓል፡፡

፰ኛ/ በተጠናከረ ሁኔታ በደብሩ ውስጥ ይሰጥ በነበረው የሰብከተ ወንጌል አገልግሎት እማካይነት ለአካባቢው ሕዝብ ከፍተኛ የሆነ ሐዋርያዊ አገልግሎት አበርክቷል፡፡ ከስብከተ ወንጌል አገልግሎት በተጨማሪ የእመቤታችንን የቅድስት ድንግል ማርያምን ውዳሴ በመተርጐም በኩል ያደርግ በነበረው ልባዊ ተሳትፎ ለሌሎችም የሚተርፍ ምስክርነት አግኝቶበታል፡፡ በአንድ ወቅት እማሆይ ታዬች የተባሉ በግቢው ውስጥ ይኖሩ የነበሩ አዛውንት መነኩሲት በፍልስታ ጾም ወቅት በሴቶች በር አንጻር ቆመው እየጸለዩ ሳለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደተገለጠችላቸውና "አያሌው ውዳሴ ማርያም ሲያደርስ ለማድመጥ ነው የመጣሁት እንዳለቻቸው፡፡" መናገራቸውን ብዙዎች ያውቃሉ፡፡

አባቴ ከተክለሃይማኖት ደብር አስተዳዳሪነቱ በተጓዳኝ የቤተ ክህነቱን የሲቃውንት ጉባዔ ሰብሳቢነት ሥራውንም በአግባቡ ይወጣ ነበረ፡፡ በሁለቱም በኩል የሚያደርጋቸው ተሳትፎዎች እንዲያው ሠርቶ ደመወዝ ለማግኘት ብቻ የሚያከናውናቸው ሳይሆን ገና ከወጣትነት ዕድሜው ጀምሮ ዓላማ አድርጐ የያዛቸውን ዕቅዶቹን ከማስፈጸም አንጻር የሚተገበሩቸው ነበሩ፡፡

በምዕራፍ ፀሥራ እንድከጠቀስናቸው የተግባር መመሪያዎቹ መካከል በተራ ቁጥር አንድ የተመለከተውን ዓላማውን ከፍጻሜ ከማድረሱ በፊት በእንጦጦ የስዊድን ወንጌላዊት ሚሲዮን ቆይታው የተደመደመ ቢሆንም በሁለቱ ዓመት ቆይታው ባገኘውና ጓደኛውና ተማሪው አቶ አስፋው ባደረጉለት ድጋፍ የእንግሊዘኛ ብሬል መጻሕፍትን ማንበብና በብሬል መጻፍን በአግባቡ ይከውን ነበረ፡፡

በትራ ቁጥር ሁለት ላይ ይዞት የነበረውን ዓላማ በተመለከተ በጊዜው ብዙ ሥራ ሠርቷል፡፡ ለእብነት ያህል የዎች ታዎር ሚሲዮንን እምነት ለማስፋፋት ይሰሩ ከነበሩ ሰዎች ጋር ያደረገው ፍልሚያ እንደምን በድል እንደተጠናቀቀ በዚሁ መጽሐፍ ተዘርዝሯል፡፡ በዚህ ረገድ በጣም ብዛት ያላቸው ተጋድሎዎች የፈጸመ ሲሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በተለይም ደግሞ ወጣቶች በአዲስ መጤ ሃይማኖቶች እየተጠለፉ እንዳይጠፉ ባደረገው ጥረት ውጤት አግኝቷል፡፡

አባቴ ትምህርት ማግኘትና መዳን የሚሻ ሰው ካገኘ የቁጥር ማነስና መብዛት አይመርጥም ነበር፡፡ አንድ ነጠላ ሰውም እንኳ ቢሆን እንደ ከፍተኛ ጉባኤ ትኩረትና ጊዜ ይሰጠዋል፡፡ በግለሰብ ደረጃ ትኩረትና ትምህርት ሰጥቶ ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ካመጣቸው ብዙ ሰዎች መካከል የአንዱ ግለሰብ ታሪክ እንደሚከተለው ነበር፡፡

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ወደ ውጪ ተልከው ከተማሩ ኢትዮጵያውያን መካከል እንግሊዝ አገር ከሚገኘው የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ጨርሰው የመጡ አንድ ምሁር ነበሩ፡፡ እኚህ ሰው የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የነበሩ ሲሆን ከአቶ እሰፋው በላይ ጋር በነበራቸው ቅርርብ የተነሳ ስለ ሃይማኖት ጉዳይ እብዝተው ይወያዩ ነበር፡፡ ከብዙ ውይይት በኋላ ከአቶ እሰፋው አቅም በላይ የሆነ ማብራሪያ በመፈለጋቸው ከአባቴ ጋር እንዲተዋወቁ ተደረገ፡፡ አባቴና ሰውዬው ተከታታይነት የነበረው መደበኛ መርሃ ግብር በመያዝ ለወራት የዘለቀ ውይይትና ክርክር ካደረጉ በኋላ እኚህ ሰው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ላይ ለነበሯቸው ጥያቄዎች ሁሉ መልስ በማግኘታቸው ወደ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ እምነት ተመለሱ፡፡ በዚሁ መሠረት ወደ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ተጠመቁ፡፡ የጥምቀት ሥርዓት በተፈጸመላቸው ዕለት የቅዳሴውን ሥነ ሥርዓት ተሳትፈው በካህኑ እጅ ቅዱስ ቁርባን እየተቀበሉ ሳሉ ራእይ ተገልጦላቸዋል፡፡ ካህኑ ነጭ በግ ሲለዋና

ከታረደው ነጭ በግ የፈሰሰው ደም ዲያቆኑ ወደ ያዘው ጻሕል ሲንቆረቆር ምሥጢር ተገልጦላቸው አይተዋል፡፡

በተራ ቁጥር ሦስት ላይ አስቀምጠት የነበረ ዓላማውን በመተግበር ረገድ ከግለሰብ አልፎ ህብረተሰቡ በደስታም ሆነ በኀዘንበሚሰባሰብበት በማንኛውም መድረክ ላይ ከተገኘ ከምእመናን ዕለታዊ ሕይወት ጋር በማዛመድ ስብከተ ወንጌል ያስተላልፍ ነበር፡፡ ሠርግም ይሁን ለቅሶ በሰለቱ ከሆነውና ሊሆን ከታቀደው ሁኔታ በመነሳት ስብከተ ወንጌልን ከምእመናን ዕለታዊ ሕይወት ጋር በማዛመድ ስብከተ ወንጌል ያስተላልፍ ነበረ፡፡ በዚህ አገልግሎቱ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ማኅበረ ምእመናን ስለሃይማኖታቸው ጠለቅ ያለ ዕውቀት እንዲኖራቸውና ከአጥማጆች ራሳቸውን እንዲጠብቁ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖትን ዐውደ ምሕረትና ጸሎ ፍልሰታን፤የቅዱስ እስጢፋኖስን፤የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለምን ምድረ ግቢዎችና ዕለተ ሰቅለትን፤ የቁስቋም ማርያምን ቤተ ክርስቲያንንና የእመቤታችንን የስደቷን መታሰቢያ፤ ብሥራተ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንንና የታህሣሥ ገብርኤልን በዓል፤ መስቀል አደባባይንና የመስቀል በዓልን፤ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን እና የሚያዚያ ጊዮርጊስን በዓል፤የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያንና የብሔራዊ ጸሎት ጥሪ፤ የወታደራዊው መንግሥት ትዕዛዝና የጉጃም ጉዞ እንዲሁም ስማቸው ያልተጠቀሰ በሌሎች አድባራትና ገዳማት ያስተማራቸውን ትምህርቶችና ታዋቂ ንግግሮቹን በአድናቆትና በእርካታ ሲከታተል የኖረው ህዝብ "የኢትዮጵያውያን ሕሊና" "ሊቀ ሊቃውንት" "አራት ዓይና" "ልበ ብሩህ" የተሰኙ የፍቅርና የአክብሮት ተቀጥላ ስሞችን ሰጥቶታል፡፡

አባቴ በሚያስተምረው ትምህርት ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ይህ ቀረሽ የማትባል መሆኗን ምእመናን እንዲገነዘቡና የሌላ እምነትም አንጻይናፍቁ አጥብቆ ይመክር ነበረ፡፡ የኢትዮጵያን ሥነ መንግሥታዊ ችግር በተመለከተም ማንኛውም ችግር መፈታት የሚችለው እንደ ሸቀጣ ሸቀጥ ከውጪው ዓለም ተጭኖ መጥቶ በሚራገፍ ፍልስፍናና ሥነ መንግሥታዊ ዘይቤ ሳይሆን የአገሪቱንና የሕዝቧን

ታሪክና ጥንተ ተዘምዶ፥ ነባር ባህል፥ ሕግና ሥርዓት በእርጋታ አቀንቶ፥ ባለአገሩን ሕዝብ አማክሮና አድምጦ፥ የጐደለውን በመሙላት የጠመመውን በማቅናት ወደ ሥልጣኔ ጐዳና መምራት ይቻላል፡፡ አሰበለዚያ ግን በመሠረት ላይ ያልታነጸ ጊዜአዊ ግንባታ ይሆንና ዘወትር ሲንዱ ሲገነቡ መኖር ይመጣል የሚል ነበረ፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ በዓለም ካሉ አገሮች ሁሉ ልዩ ሆና የምትገኝበትን ከፍጥረት ጥንት ጀምሮ በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ የነበረች፥ ያለችና የምትኖር ሀገረ እግዚአብሔር መሆኗን ያለማንገራገር መቀበል ካልተቻለ በላምን፥ አንድነትንና ብልጽግናን አግኝቶ መኖር ዘበት መሆኑን አጠንክሮ ይናገር ነበረ፡፡

በአራተኛ ተራ ይዞት የበረውን ዓላማውን በተመለከተ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ያቀረባቸው ሲሆን የመንፈሳዊ መልእክቶች ይዘት በአብዛኛው በዘመናዊው ትምህርት አቅጣጫ ላይ ያተኮሩ፤ ዘመናዊነት፣ ኢትዮጵያዊነትና ሥልጣኔ የተባሉት ጉዳዮች በወጣቱ ሕይወት ውስጥ የፈጠሩት ተቃርኖ በአገሪቱ በህዝቡና በመንግሥት ላይ ሲያስከትል የሚችለውን መዘዝ ጭምር የመጠቆም ሐሳብ ያሰባቸውና መንፈስ እግዚአብሔር የተገለጠለትን ያህል አስቀድሞ ለመናገርና ለማስጠንቀቅ የሞከረባቸው ናቸው፡፡

ፊታቸው በቀረበ ቁጥር በሚያቀርበው ትችና ጠንካራ መልእክት የተገረሙት ንጉሠ ነገሥት በአንድ ወቅት "ሁሉ ይፈራናል ያከብረናል አንተ ለምንድን ነው የማታከብረንና የማትፈራን?" ብለው ጠየቁት፡፡ እሱም "...የግርማዊነትዎን ሞገስና የዙፋንዎን ግርማ በዓይነ ስጋርነቴ ምክንያት ባለማየቴ ይሆናል፡፡ ለእኔ የሚታየኝ የሚያስፈራኝና የሚያንቀጠቅጠኝ የሰማያዊው ንጉሥ የኢየሱስ ክርስቶስ ዙፋንና ግርማ ነው፡፡..." ብሎ መልስ ሰጥቷቸዋል፡፡

በመንፈስ እግዚአብሔር እየተመራ በዓይነ ትንቢት ያየውን የንጉሡ ነገሥቱን ፍጻሜ በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. አፈታቸው ቆሞ ሲናገር ከእሱ በቀር ለሌሎች ትርጉም ያለው የማይመስል የነበረው ጉዳይ በእውን ተፈጽሞ በማየቱ አጅግ አድርጎ ያዝን ነበረ፡፡ በግንቦት ወር ፲፱፻፷፮ ዓ.ም.

ውስጥ በትክክል በማላስታውሰው ቀን ወደ ማታ ላይ ከደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን የተላኩ ሰዎች እየተሯሯጡ መጥተው ጃንሆይ መምጣታቸውንና አባቴን እንደሚፈልጉት ነገሩት፡፡ እሱም በችኮላ ልብሱን ለውጦ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደ፡፡ ከተወሰኑ ሰዓታት በኋላ ወደ ቤት ሲመለስ በከፍተኛ ኃዘንና ትካዜ ውስጥ ነበረ፡፡ ለምን እንደፈለጉትና ምን እንደገጠመው ስጠይቀው "ስትናገር የነበረው ሁሉ ደረሰ፡፡ አገር እየተረበሸ ካህናት ተኝተዋል? አይጸልዩም?" ብለው እንደጠየቁት ነግሮኛል፡፡ በዚያ ቅጽበት ግርማዊነታቸው የተናገሩትን ብዙ ጊዜ እያስታወሰ ያዝን ነበረ፡፡



# አብዮቱ፣ ቤተ ክህነትና አባቴ

በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. የተከሰተው የለውጥ ማዕበል አንገት ለይቶ ከወጣ በኋላ "አብዮት" የሚል ስያሜ ተሰጠው፡፡ የጊዜው ጋዜጠኞች "አብዮት" የሚለው ቃል የግእዝ ቋንቋ መሆኑ ሳይጠፋቸው የአማርኛ ትርጉሙ ተሰወራቸው፡፡ ይህንን ስም ያወጡለትን የቤተ መንግሥት ሰዎች መጠየቅ ትተው የግእዝ ባለሙያዎች ወደ ነበሩበት ወደ ቤተክህነት ግቢ ጐራ አሉ፡፡ የግእዝ ቋንቋ ተርጓሚ ፍለጋ ሲያጠያይቁ ወደ ሊቃውንት ጉባኤ ቢሮ ቢሄዱ እንደሚሻል ተነገራቸው፡፡ ወደ ሊቃውንቱ ጉባኤ ሄዱ፡፡ የጉባኤው ሰብሳቢ የነበረውን አባቴንና አባላቱን አገኙ፡፡ ሰላምታ አቅርበው የመጡበትን ጉዳይ ካስረዱ በኋላ፤ "አለቃ! አብዮት ማለት ምን ማለት ነው? ብለው አባቴን ጠየቁት፡፡ አባቴም መለሰ ፤"አብዮት፣ አበየ ከሚለው ሥርወ ቃል ይወጣል፡፡ 'አበየ' ማለት እምቢ አለ ማለት ሲሆን፤ 'አብዮት' ማለትም እምቢተኝነት ነው፡፡" ብሎ ተረጐመላቸው፡፡

ይሄ አብዮት ዒላማ ካደረጋቸው ተቋሞች መካከል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀንደኛዋ ነበረች፡፡ ይህም የሆነው በቤተክርስቲያኒቱ፣ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውን ምንነትና ማንነት ላይ ያላትን ታሪካዊ ሚና እንዲሁም ብሔራዊት መሆኗን ባለማስተዋል ይደረጉ በነበሩ ቅስቀሳዎች ምክንያት ነው፡፡ በወቅቱ ይታዩ ከነበሩ እንቅስቃሴዎች አንዱ ቤተ ክርስቲያኒቱን በመቃወም ወደ አደባባይ በሰልፍ መውጣት ነበረ፡፡

አባቴ በጊዜው አደገኛ ሊሰኝ የሚችል ንግግር አድርጓል፡፡ የአገር ግዛት ሚኒስቴር ይባል ከነበረው መሥሪያ ቤትና በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ከነበሩት ከልጅ እንዳልካቸው መኰንን ፊት ቀርቦ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ የቀረቡ ተቃውሞዎች አግባብነት የሌላቸው መሆናቸውን በመግለጥ መንግሥት የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች በጥንቃቄና በአግባቡ እንዲመለከታቸው አስገንዝቧል፡፡ በጊዜው ከነበረው የለውጥ ፍላጐትና የአብዮቱ ማዕበል ካስነሣው ወጀብ አንጻር ሲታይ ሕይወቱን ከፍተኛ አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ንግግር ነበረ፡፡

የወታደራዊው መንግሥት ዘመን ብዛት ያላቸው በውጪ አገሮች የተማሩ ሰዎች ወደ ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣንና ማዕረግ የመጡበት ዘመን ነው፡፡ ቢሆንም የተማረ ሰው እንደ መብዛቱ መጠን ቤተ ክርስቲያኒቱ ጠንክራ መገኘት ሲገባት ይበልጥ ተሽኮርማሚና ለባለ ሥልጣንና ለባለ ጉልበት እንገቷን አቀርቅራ የተገዛችበት ዘመን ሆኖ አልፏል፡፡

ወታደራዊው መንግሥት የመጀመሪያውን ፈተና ለቤተ ክርስቲያን ያቀረበው ተሐድሶ ጉባኤ ተብሎ የሚጠራ ኮሚቴ በማቋቋም ነው፡፡ የኮሚቴ አባላት ሆነው ከተሰየሙት መካከል ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም፣ አለቃ አያሌው ታምሩ፣ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፣ ቄስ ጻዎቸው ካሣሁን፣ ዶክተር ክነፈ ርግብ ዘለቀ፣ አቶ ፍቅረ ድንግል በየነ፣ አቶ መርስዔ ሐዘን አበበ፣ አቶ እጅምሮ ወንድም አገኘሁና ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ነበሩ፡፡ እንሁም ሊቃነ ጳጳሳት በአባለነት ይገኙበት ነበር፡፡

የኮሚቴው አባል የነበሩት ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ "እንድ አፍታ ላውጋችሁ" በሚል ርእስ በጻፉት የሕይወት ታሪካቸው ላይ እንዳሰፈሩት ወታደራዊው መንግሥት ይህንን ኮሚቴ ሲያቋቁም የሰጠው ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ ወጥታ ራሷን የምትችልበትን መንገድ ለማቋቋም ነው የሚል ነበረ፡፡[47] ምንም እንኳ ኮሚቴው የተቋቋመበት ምክንያት ግልፅ ቢሆንም በጉባኤው ስብሰባዎች ላይ ይነሡ የነበሩ አጀንዳዎች ግን ከዋናው ምክንያት ያፈነገጡና የቤተ ክርስቲያንን ቀኖናና ሥርዓት የጣሱ ነበሩ፡፡

በኮሚቴው ውስጥ ከነበሩት ሰዎች መሐል በጐ ያልሆነ ዓላማ ይዘው የሚንቀሳቀሱ አባላት ቅዱስ የፓትርያርኩን ሥልጣን የሚጋፉ አጀንዳዎችን በማንሣት መንግሥት ፓትርያርኩን ለማሰር ወይም ከሥልጣናቸው ለማውረድ ለነበረው ዕቅድ መንገድ ያመቻቹ ነበር፡፡

[47]ጌታቸው ኃይሌ፤እንዳፍታ ላውጋችሁ፤፲፱፻፺ ዓ.ም.



ይህም በጉባኤው አባላት መካከል ውዝግብና ልዩነት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኖ ነበር፡፡ ከባድና አወዛጋቢ ከነበሩት ጉዳዮች አንዱ ከቤተ ክርስቲያን ቀኖናና ሥርዓት በተጻራሪ ቅዱስ ፓትርያርኩ ጳጳሳትን ለመሾም ይዘውት የበረውን ዕቅድ እንዲለውጡ ለመጠየቅ ኮሚቴው መነሣቱ ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ በቅዱስ ፓትርያርኩና በሲኖዶስ ሥልጣን ውስጥ መግባት ከሕገ ቤተ ክርስቲያን ውጪ የሆነ እንቅስቃሴ መሆኑን ከዚያም አልፎ የቤተ ክርስቲያንንና የመላው ክርስቲያን ምእመናንን ክብር መንካት መሆኑን በመግለጥ በአቋም ከሚመስሉት ጋር ሆኖ አባቴ ተቃውሞውን አሰማ፡፡ሆኖም ግን ቅዱስ ፓትርያርኩ ጳጳሳትን እንዳይሾሙ የሚፈልገውክፍል በድምፅ ብልጫ በማሸነፉ የብዙኀኑን አቋም የሚገልጠው ደብዳቤ ለቅዱስ ፓትርያርኩ ተላከ፡፡ ይህንን ጉዳይ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ከላይ በጠቀስኩት መጽሐፋቸው ላይ ገልጠውታል፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ቴዎፍሎስ የኮሚቴውን ጣልቃ ገብነት ወደ ጐን በመተው በታቀደው መሠረት የጳጳሳቱን ሹመት አከናወኑ፡፡ ከሹመቱ በኋላ እሳቸውም የተሾሙት ጳጳሳትም ለእስራት ተዳረጉ፡፡ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ቴዎፍሎስ ከታሰሩ በኋላ አባቴ በጉባኤው ውስጥ መቆየት እንደማይፈልግ ገልጾ ራሱን ከአባልነት አገለለ፡፡ የጉባኤው የበላይ ተቆጣጣሪ የነበሩት የደርጉ ምክትል ሊቀ መንበር ኮሎኔል አጥናፉ አባተ በአባቴ ድርጊት በመበሳጨታቸው የወቀሰና የዛቻ ደብዳቤ ጻፉለት፡፡ ይኸው ደብዳቤ"ጥብቅ ምሥጢር" የሚል በቀይ ቀለም በጉልህ የተጻፈ ልዩ ምልክት ተደርጐበት በግል ማኅደሩ እንዲቀመጥ ተደረገ፡፡

ከተሐድሶ ጉባዔ ለቤተ ክህነት በቀረበ ጥያቄ መሠረት አባቴ ከተሳተፈባቸው ዓበይት ጉዳዮች አንዱ የቤተክርስቲያን ዘላቂ መተዳደሪያ በጀት ጉዳይ ነበረ፡፡ ለዘመናት የሲሶ መንግሥት መተዳደሪያ የነበራት ቤተ ክርስቲያን ወታደራዊው መንግሥት የገጠርና የከተማ ቦታዎችን ሲወርሱ ያለምንም መተዳደሪያ የቀረችበት ጊዜ

ነበረ፡፡ ጊዜያዊው ጉባዔ ለችግሩ መፍትሔ የሚሆን ጥናታዊ ሐሳብ አምጡ የሚል ጥያቄ ለቤተ ክህነቱ ኃላፊዎች አቀረበ፡፡ በጥያቄ መሠረት ጉዳዩን ያጠናው ኮሚቴ ከመስከረም ፩ እስከ መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ድረስ ባደረገው ጥናት ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ የሆነ ሰነድ አዘጋጅቷል፡፡ ኋላ ላይ ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደርበት በጀት ከመንግሥት ሊፈቀድ የቻለው በዚህ ሰነድ አማካይነት ነው፡፡ በወቅቱ የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢና የታሪክና ሥነ ጽሁፍ ማደራጃ መምሪያ ሥራ አስኪያጅ የነበረው አባቱ ከላይ የተጠቀሰው ጥናት ሲሠራ የቤተ ክርስቲያንን ብሔራዊትነትና ለአገርና ለወገን ያበረከተችውን አስተዋጽኦ ጉልህ አድርጐ ከማሳየት ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡

አባቱ ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩ ሰሞን ከላይ በተገለጠው የጥናት ቡድንና በጊዜያዊ ጉባኤው ውስጥ አባል የነበሩ አንድ ሰው የጥናቱን ጽሁፍ ሰጥተውኛል፡፡ በተጨማሪም "...ይህ ጽሁፍ የአባትሽ የእእምሮ ውጤት ነው፡፡ ምናልባት እሳቸው በኮሚቴው ውስጥ ባይኖሩ ኖሮ የቤተ ክርስቲያንን ታሪካዊ አስተዋጽኦና ምንነት እንዲህ ጉልህ ሆኖ አይወጣም ነበረ፡፡ ይህንን ሰነድ በማዘጋጀት ረገድ አባትሽ ለቤተ ክርስቲያን የሠሩት ውለታ እጅግ ታላቅ ነው፡፡ በመሆኑም እንደ ታሪካዊ ሰነድ ልትይዢው ይገባል"በማለት ሰጥተውኛል፡፡

ከሰነዱ እንደተረዳሁት የጥናቱን ሥራ በሰብሳቢነት የመሩት በወቅቱ የቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ክቡር አቶ ተድላ ዘዮሐንስ ሲሆኑ መልአከ ገነት በጽሐ ጌታሁን፣ አለቃ አያሌው ታምሩ፣ አቶ ጌታሁን ዘውዴ፣ አቶ ጌታቸው ገብሬ፣ አቶ ሳሙኤል ቤተ ማርያም፣ አቶ አፈወርቅ ወልደ ኪሮስ፣ ዶክተር ሐዲስ የሻነው፣አቶ ታምራት አበራ፣ አቶ ብርሃኑ አደመ፣አቶ ተሾመ አለማየሁና ቄስ ክፍሌ ገብረ መስቀል ደግሞ የጥናት ጉባኤው አባላት ነበሩ፡፡

ጥናቱ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቦ ብፁዕ ወቅዱስ ፖትርያርክ አቡነ ቴዎፍሎስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባሎች ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት በነበሩበት የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ክቡር አቶ ተድላ ዘዮሐንስና የጥናቱ



አባሎች በአስረጅነት በተገኙበት መስከረም ፳ እና ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ውይይት ከተደረገበት በኋላ ቅዱስ ሲኖዶስ ተስማምቶበት አሳልፎታል፡፡

"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሳይቋረጥ እንዲቀጥል ለማስቻል የተደረገው ጊዜያዊ ጥናት" የሚል አርዕስት በተሰጠው ሰነድ እንደሚያሳየው ለጥናቱ መነሻ የሆኑት ጉዳዮች፣

፩) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን በመዓልትና በሌሊት ሳታቋርጥ ስታከናውን የኖረችውን መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲከናወን ያስቻለው አስተዳደራዊ መዋቅር ተደግፎ የኖረበት የገጠር መሬትና የከተማ ቦታ በወታደራዊው መንግሥት መወረሱና፣

፪) የቤተ ክርስቲያን ዘለቄታዊ አቋም ጥናት ተጠናቆ የራሷ የሆነ የተስተካከለ አመራርና ከጊዜው ጋር የሚራመድ አስተዳደር እንድትጨበጥ ለማብቃት እስኪቻል ድረስ በመሸጋገሪያው ወቅት ቤተ ክርስቲያን ችግር እንዳይደርስባት ለመርዳት አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን መንግሥት ያመነበት በመሆኑ ነበር፡፡

ጉባኤው ጥናቱን በሚሠራበት ወቅት ከፍተኛ ትኩረት ያደረገባቸው ነጥቦች ፤

ሀ) ቤተ ክርስቲያን እስከዚያ ጊዜ ድረስ አገልግሎት ስታከናውንባቸው የነበሩ የሀብት ምንጮችን መመርመር፣

ለ) የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚቀጥልበትን ጊዜያዊ ጥናት ስለመቀጠል፣

ሐ) ቤተ ክርስቲያን ወደ ፊት ራሷን ችላ የምትተዳደርበትን ሁኔታ ማጥናት፣

ሲሆኑ ስለ ቤተ ክርስቲያን ህልውና፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነት፣ ስለ አገልጋዮቿ ብዛትና ስለሚያስፈልጋት የመገልገያ ንብረቶችም ጥናቱ አካቶ ነበር፡፡

ሰነዱ እንደሚገልጠው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከሕዝብ ወጥታ ለሕዝብ አገልግሎት የቆመችው ነች፡፡ በሕዝብ አንድነት የተገነባች፣ ለሕዝብ ቀዋሚና ዘላቂ ሕይወት ስትሠራ የኖረችና የምትኖር፣ ግዙፍና ረቂቅ፣ ጊዜያዊና ዘለዓለማዊ ኃይልና ሕይወት ያላት ቀዋሚት የሕዝብ ድርጅት፣ መንፈሳዊት የእግዚአብሔር መንግሥት ናት፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከሕገ ልቡና እስከ ሕገ ወንጌል ያደረገችው ጉዞና ከምኩራብ ወደ ቤተ መቅደስ የደረሰችበት ቅርጽ ሲታይ የጥንታዊነቷንና የአገልግሎቷን ቀዳሚነት የሚያስገነዝብ ነው፡፡ከዚሁ ጥንታዊ አገልግሎቷ የተነሳ ኢትዮጵያ ወይም ቤተ ክርስቲያን ብሎ በመጥራት መካከል ልዩነት የሌለ መሆኑንም ይኸው ሰነድ ያስገነዝባል፡፡ ይህንኑ የተገነዘቡ ጥንታውያን ታሪክ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያን "የአምላክ አገር"፣ ብለው እስከ መጥራት የደረሱ መሆኑን ገልጦ ዓለምም "የክርስቲያን ደሴት" እያለ የሚጠራት ከዚሁ ታሪካዊ እውነታ በመነሳት መሆኑን ያብራራል፡፡ በተለይም ደግሞ " ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" ተብሎ በቅዱስ ዳዊት የተነገረው ምሥክርነት በመጽሐፍ ቅዱስ የሰፈረና ከላይ ለተባለው ሁሉ ዋንኛ ማረጋገጫ መሆኑ በሰነዱ ላይ ተገልጧል፡፡

የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎትና ባለውለታነት አስመልክቶ ሰነዱ በጥቂቱ ካስፈራቸው ነጥቦች መካከል የሚከተለው ይገኛል፡፡

"...ሀገር ወይም ብሔር፣ ሀገርነት ወይም ብሔርነት እንዲሁም የሀገር ገንዘብ የሆነ ሁሉ ማለትም ፊደል፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ባህል፣ ሥነ ሥርዓት፣ ሕግ፣ ሥነ ጽሕፈት፣ ኪነ ጥበብ፣ ሥነ ጥበብ፣ ቅኔ፣ ዜማ፣ ሙዚቃ፣ ትምህርት፣ አስተዳደር፣ ባለአገርነት፣ ተባብሮ መሥራት ወይም የሕዝብ አንድነት፣ መንግሥት፣ ታሪክ፣ ነፃነት፣እኩልነት፣ መስዋዕትነት ይህና ይህን የመሳሰለው ሁሉ፣ በጠቅላላውም ለአንድ ብሔራዊ ዓላማ



ተባብሮ መቆምና የሚያስፈልገውን የጊዜ፣ የዕውቀት፣ የሀብትና የሕይወት መስዋዕትነት አጣምሮ ማቅረብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለልጆቿ ለኢትዮጵያውያን በእኩልነት ያወረሰችው ከፍተኛ ሀብት ነው፡፡ ..."

ኢትዮጵያ ከጥፋት ውሀ በፊት ከነበሩ ሰዎች የተወረሱን የቀናት፣ የወራት፣ የዘመናት አቆጣጠርን፣ የግዕዝ ቋንቋንና፣ ፊደልን የመሳሰሉ የታሪክና የባሕል ቅርሶችን ይዛ የመገኘቷ ምሥጢር የቤተ ክርስቲያን ውለታ መሆኑን ሰነዱ ላይ የተጠቀመ አንዱ ነጥብ ነው፡፡ የአክሱም ሐውልት፣ የጎንደር ቤተ መንግሥት፣ የላሊበላ ሕንጻዎች፣ በልዩ ልዩ ቦታዎች ከመሬት በላይም ሆነ ከመሬት በታች የሚገኙና እየተፈለጉና እየተቆፈሩ በመውጣት ላይ ያሉ ቅርሶች ሁሉ የቤተ ክርስቲያን በረከቶች መሆናቸው በሰነዱ የተብራራ ሲሆን ከላይ የተዘረዘሩትን ቅርሶች የወረሱ ኢትዮጵያውያን ሁሉ (የዕምነቷ ተከታይ ቢሆኑም ባይሆኑም) የቤተ ክርስቲያን ውለታ እንዳለባቸው፣ ውለታ ብቻም ሳይሆን ራሳቸውም የቤተ ክርስቲያን መሆናቸው ተብራርቷል፡፡

በዚሁ ሰነድ ውስጥ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነት በተጠቀሰበት ክፍል ውስጥ "...የመንግሥት ሥልጣን የሚመነጨው ከህዝብ ነው፡፡ የህዝብ አንድነትና ሕይወትም ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሥረ ወጥ የሆነ ግንኙነት አለው፡፡ ስለዚህ ምንጊዜም ቢሆን የኖረችው፣ ያለችውና ወደፊትም የምትኖረው ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ አስፈላጊ ናት፡፡ ..." የሚል ማብራሪያ የሚገኝ ሲሆን በኢትዮጵያና በሌሎች አገሮች በሚገኙ የቤተ ክርስቲያን ተቋሞች መሠረታዊ ልዩነት በተመለከተም በሌሎች አገሮች የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን የአመሠራረት አቋሞች እምልኮተ ጣዖትን ሽረው በአምልኮተ እግዚአብሔር ሲተኩ ቤተ ጣዖትን አፍርሰው ቤተ ክርስቲያን መተካታቸውን ያሳያል፡፡

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ግን ከላይ ከተገለጠው በተለየ ሁኔታ በጥንተ ፍጥረት ከነበሩ አበው ጀምሮ በሕገ ልቡና ላይ የተመሠረተ መሆኑን ይህም የቀን አቆጣጠርን፣ የዘመን መለወጫ በዓልን፣ የረቡዕና የዓርብ ጾምን በሰባት ዓመት መጀመርን በማስተዋል

በሕገ ልቡና እዚአብሔርን ያመልኩ ከነበሩ አበው የተገኙ መሆናቸው፣ በግእዝ ቋንቋ ተጽፎ በኢትዮጵያ የተገኘውና ወደ ልዩ ልዩ የዓለም ቋንቋዎች የተተረጐመውን መጽሐፈ ሄኖክን በማየት መገንዘብ እንደሚቻል ያትታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በታቦተ ጽዮን አማካይነት ሥርዓተ አምልኮተ እግዚአብሔር ሲከናወን መኖሩ፣ መልከ ጼዴቅ ለአብርሃም በረከትን መስጠቱ፣ ሙሴና ኢትዮጵያዊቷ ሚስቱ በእግዚአብሔር ዘንድ በእኩልነት መታየታቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቆመችበት መሠረት በሌሎች አገሮች የሚገኙ ቤተ ክርስቲያኖች ከቆሙበት መሠረት የተለየ አኩሪ የአምልኮ ቅርስ ለመሆኑ እማኞች መሆናቸው ተጠቅሷል፡፡

ኢትዮጵያ ሕገ ወንጌልን በተቀበለችበት ጊዜ የተፈጸመው፣ የነበረውን አፍርሳ ሌላ የማነጽ ሥራ ሳይሆን በነበረው ላይ የሚያስፈልጋትን በመጨመር ኦሪትን ከወንጌል አስተባብራ፣ በትንቢተ ነቢያት ላይ ስብከተ ሐዋርያትን አጣምራ፣ በመንፈስ ረድኤት ላይ መንፈስ ልደትን ተቀብላ፣ ከአብርሃም ፣ ከሙሴና ከጳውሎስ እኩል ሕዝቧን ስትመራ መኖሯ ተገልጧል፡፡ በአክሱም የታቦተ ጽዮንን ቤተ መቅደስ፣ በልዩ ልዩ ክፍላተ አገር ምኩራባተ ኦሪትን እየሰራች፣ መሥዋዕተ ኦሪትን እየሰዋች፣ ሕዝቧን በሕግ ስትመራ እንደኖረች ፣ ኋላም ምኩራበ ኦሪት በተሰራባቸው፣ መሥዋዕተ ኦሪት በተሰዋባቸው መቅደሶች ሁሉ ኦሪትና ወንጌል እንዲነገርባቸው፣ በኦሪትና በወንጌል የታወቀው ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር እንዲሰዋባቸው በማድረጓ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በምኩራበ ኦሪት ላይ ቆማለች በማለት በሌሎች አገር በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን የአመሠራረት ልዩነት ሰነዱ በሰፊው አብራርቷል፡፡ መንግሥት የቤተ ክርስቲያንን መብት መጠበቅ እንደሚገባው በተጠቀሰበት አንቀጽ ወስጥ ደግሞ፣

"ቤተ ክርስቲያን ባሁኑ ጊዜ ለመንግሥት የምታቀርበው ጥያቄ ወላጆች ለልጆች እንደሚያቀርቡት ጥያቄ ያለ እንጂ ልጆች ለወላጆች



የሚያቀርቡትን ጥያቄ የሚመስል አይደለም፡፡ ልጆች የሚጠይቁት የወላጆቻቸን የሆኑ ሁሉ ለኛ ሊሆን ይገባል በሚል አቅጣጫ ነው፡፡ ወላጆች ከልጆቻቸው የሚጠይቁት ግን የደከሙበትን እንዳያሳጧቸው ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት የምትጠይቀው የእሷ ያልነበረው እንዲደረግላት፣ የሌላው እንዲሰጣት፣ ያልደከመችበት እንዲመደብላት አይደለም፡፡ ጥንታዊት፣ ቀዳማዊት፣ ሕዝባዊትና ብሔራዊት በመሆን የኢትዮጵያን አቋም አስተካክላ ጠብቃ የኖረች ፣ ያለ እግዚአብሔር ተአምና ያለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ በስተቀር ከውጪ ዓለም ምንም ዓይነት ርዳታ የሌላት እንደመሆኗ መጠን ጥንት የነበረው መብቷ፣ ሀብቷ ተፈቅዶ ለሕዝብ የምታበረክተው አገልግሎት ያለማቋረጥ እንዲቀጥል ብቻ ነው፡፡" የሚል ይገኝበታል፡፡ በዚህ ታሪካዊ ሰነድ አማካይነት የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ምንነትና ማንነት ለማስገዘብ በተደረገው ጥረት ቤተክርስቲያኒቱ ምንም እንኳ የጠየቀችውንና የሚገባትን ባታገኝም ከመንግሥት በጀት ተመድቦላት ሀልዋናዋ ሳይጠፋ ለመቆየት ችላለች፡፡

በቤተ ክርስቲያን ሀልውና ላይ የመጣውን ከላይ የተጠቀሰውን ዓይነት ኃላፊነት ከመወጣት ጐን ለጐን በማስተማር ረገድም አባቴ ብዙ ደክሟል፡፡ በወታደራዊው መንግሥት ዘመን ሰፍኖ የነበረውን አምባገነናዊ አገዛዝና የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና ሥርዓት የሚቃረኑ ድርጊቶችን ፊት ለፊት በመቃወም ረገድ በብዙ ጉዳዮች ላይ ግምባሩን ሳያጥፍ ድምፁን አሰምቷል፡፡ እኔ በማስታውሰውና በጊዜው በሥራ አካባቢ አብረውት ይሠሩ የነበሩ ሰዎች እንደሚያረጋግጡት መታረም አለባቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ችግሮች በተመለከተ ያለፍርሃትና መልመጥመጥ የሚያስፈልገውን ያደርግ ነበር፡፡ ጉዳዮቹ ለቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች መቅረብ አለባቸው ብሎ ባመነ ጊዜ ያቀርባል፡፡ ለአስተዳደር፣ ለቅዱስ ሲኖዶስና ለርክበ ካህናት ጉባኤዎች ችግሮቹን በማቅረብ ለመፍትሔዎቹ ያተጋቸው ነበር፡፡ አንዳንዴም እንደ ጉዳዩ ክብደትና ቅለት በቤተሰባዊ መንፈስ የሚመለከታቸውን ብቻ ማነጋገርን

ይመርጥ ነበር፡፡ ይህንን የሚያደርገውም ሰለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ቅዱሳን አባቶች ክብር በመጠንቀቅ ነበረ፡፡

በሦስተኛው ፓትሪያርክ ዘመን የነበረው ሁኔታ ሲመዘን በአብዛኛው ክርስቲያናዊ ጥንካሬን የማጣትና ከቤተ ክርስቲያኒቱ ውጪ ለሚመጡ ጫናዎች የመንበርከክ ባሕርይ በጉልህ የሚታይበት ነበረ፡፡ ጫና ቢኖርም ባይኖርም ደግሞ በጭፍን አድር ባይነት ጭምር በርከት ያሉ ስሕተቶች ይሠሩ ነበር፡፡ ለዚህ አባባል አማኝ ከሚሆኑ ብዙ አስረጂዎች መካከል አባቴ አርምት እንዲወሰድባቸው ይጠይቅባቸው ከነበሩ ጉዳዮች መካከል ከዚህ በታች የተጠቀሱት ይገኙባቸዋል፡፡

ሀ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከሥልጣናቸው ወርደው መታሰራቸውን እንዲሁም በምትካቸው አቡነ ተክለ ሃይማኖት መሾማቸውን፥

ለ/ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ለአገር አንድነት የከፈለችው መሥዋዕትነት ተረስቶ ብዙ አብያተ ክርስቲያን እንዲዘጉ መደረጉንና ተተኪ ካህናትና ዲያቆናት የሚሆኑ ወጣቶች ወደ ወታደራዊ ኃይል እንዲገቡ መደረጉ፤

ሐ/ የሊቢያ መሪ በነበሩት መሐመድ ጋዳፊና በወታደራዊው መንግሥት መሪዎች መካከል ተፈጥሮ የነበረውን ጊዜያዊ ፍቅር ተከትሎ ከጊዜው ነፋስ ጋር ዐብረው የነፈሱ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት አነባሽነት "ሃይማኖት አይለያየንም " በሚል ርእስ መጽሐፍ ከመታተሙም በላይ በመጽሐፉ ሽፋን ላይ ቤተ ክርስቲያንን ከጉልላቷ ለይቶ ባዶ አድርጎ ከመስጊድ ጋር አገናኝቶ የተሣለ ሥዕል የነበረበት መጽሐፍ ታትሞ መበራጨቱ፤

መ/ "የኮሚኒስት ማኒፌስቶ" እየተባለ የሚጠራው መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያኒቱ ማተሚያ ቤት ታትሞ መሰራጨቱና "የወንጌል ትምህርትና ሶሻሊዝም አንድ ናቸው"፣ "የኮሚኒስት ሥርዓት የሐዋርያት ሥርዓት ነው"፣ "ሰው የእግዚአብሔር የሥራ ውጤት ነው"፣ "ከሀገር ወዲያ



ሃይማኖት የለም"፣ "ስኢትዮጵያ በአብዮቱ የተጠመቁ ጳጳሳት ያስፈልጓታል" የሚሉና ሌሎችም የክሕደትና የመናፍቅነት ስብከቶች አስመስሎ ማደር በተጠናወታቸው አንዳንድ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች እጅ እየተጻፉ የቤተ ክርስቲያን ልሳን በሆነው በዜና ቤተ ክርስቲያን ታትመው እንዲወጡ መደረጉ፤

ሠ/ የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች፥ ቀሳውስትና ዲያቆናት መዘምራንና ማኅበረ ምእመናን እንዲሁም የወቅቱ ፓትሪያርክ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በተገኙበት ጉባኤ ላይ በስብከተ ወንጌል አዳራሽ ውስጥ " እሮጌይቱ ቤተ ክርስቲያን ትውደም፥ አሮጌው ሲኖዶስ ይውደም፥ ሲኖዶስ ቅዱስ አይባልም" የሚሉ መፈክሮች በራዪ በቤተ ክርስቲያን አባላት እንደበት መነገሩና የነበረው ሲኖዶስም እንዲፈርስና ጳጳሳቱም ጡረታ እንዲወጡ መደረጉን፤

ረ/ የቀበሌና የገበሬ ማኅበራት ሹማምንትና አባላት በመሆን ቀይ ሽብርና ነጭ ሽብር የተባለ ስያሜ ተበጥቶላቸው ወገንን ከወገን ባጫረሱት የእርስ በርስ መጠፋፋት አጸያፊ ተግባራት ውስጥ እጃቸውን ያስገቡ ካህናትና ዲያቆናት የሰውን ደም ባፈሰሱበት እጃቸው የወልደ እግዚአብሔርን ሥጋና ደም ለማቀበል መድፈራቸውን፤

ሰ/ የአጽዋማት ራስ በሆነው በዓቢይ ጾም ወቅት "የእናት አገር ጥሪ" እየተባሉ በየአካባቢው ይደረጉ በነበሩ የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐ ግብሮች ላይ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ ይገኙ የነበሩ የቤተክህነቱ ባለሥልጣናትና የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሳይቀሩ እየተገኙ ዕርድ ሲባርኩ፥ መስቀል ሲያሜርቱ መገኘታቸውን፤

ሸ/ በቤተ ክህነቱ ከፍተኛ የሥልጣን ደረጃ ላይ ከነበሩት መሐል ራሳቸውን ለኮሚኒስት ፖለቲካ አቀንቃኞች ማድረጋቸውን በተጨማሪም የቤተ ክህነቱን ሠራተኞች በስብከተ ወንጌል አዳራሽ እየሰበሰቡ የአጋእዝተ ዓለም ሥላሴን ስም አጠራር "በስመ ማርክስ፥ ኤንግልስ

ወሌጊያ በግል የፌዝ ቃላት በመተካት ማላገጣቸውን በመቃወም
በተለያዩ መድረኮች ላይ ተቃውሞውን ገልጧል፡፡

እምልክተ እግዚአብሔር በተቃለለበት በዚያን ዘመን እንኳን መንግሥቱ
የሚያራምዳቸውን አቋሞች መቃወም ቀርቶ ሃይማኖታዊ ሆኖ መገኘ
በራሱ የሰውን ሕይወት ከፍተኛ አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ነበር፡፡
ሁኔታው ይህን ቢመስልም አባቴ ግን በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን
የጀመረውን ሐዋርያዊ ተጋድሎ አጠናክሮ ከመቀጠል በስተቀር ወደ ኋላ
አላለም፡፡

አባቴ ካስተማራቸው ትምህርቶች፣ምክሮችና ተግሣጾች መካከል እኔ ራሴ
በቦታው ተገኝቼ የተከታተልኳቸውን፣ ከሌሎች ሰዎ ያገኘኋቸውን
በጥቂቱ ለማቅረብ ሞክሬያለሁ፡፡ ጊዜው ከመራቁ አኳያ አባቴ
እንደተናገረው ቀጥታ ቃል በቃል ማቅረብ ይከብዳል፡፡ ይሁን እንጂ
ትምህርቶቹና ሁኔታው አሁንም በአዘነ ኅሊናዬ ተቀርጸው ስላሉ ፍሬ
ሐሳቦቹን ጨምቆ ማቅረብ አይሳነኝም የሚል እምነት አለኝ፡፡ እነዚህ
ትምህርቶች በተላለፉባቸው ወቅቶችና ቦታዎች የተገኙ ምእመናን ሁሉ
ለትውስታዬ ምስክር እንደሚሆኑኝ አልጠራጠርም፡፡

የ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. አብዮት የፈጠረው የለውጥ ስሜት ትንሹንም
ትልቁንም በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ በመነካካቱ፤ ወዛደሮች በባለ
ጸንቾ፣ ገባሮች በባለ ርስቶች ላይ እያመጹ የተነሡበት ጊዜ ነበረ፡፡
"ቤተ መንግሥቱ ሲሞቀው እኛን ወበቀን" ማለት ያኔም የአንዳንድ
የቤተ ክህነት ሰዎች ጠባይ ነበረና በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትም
ረብሻዎች ይታዩ ነበር፡፡

የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችም ከአብዮቱ
መንፈስ ተሳታፊ ስለ ነበሩ እራሳቸውን ከተጨቋኞች፣ አባቴን ደግሞ
ከጨቋኞች ጐራ ፈርጀው ረብሻ ጀመሩ፡፡ የጊዜው ሁኔታ እጅግ
አስቸጋሪ፣ ሕግና ሥርዓት የሌለበት ስለነበረ ጠቅላላ ሁኔታውን ግምት
ውስጥ በማስገባት አባቴ ራሱን ከአስተዳዳሪነት ሥራው አገለለ፡፡ በዚህ
የተነሣ በቤተ ክህነቱ የቢሮ ሥራ ብቻ ተወሰነ፡፡

ሆኖም ግን በአዲስ አበባ ከሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች፣ የበላይ ኃላፊዎችና የመንፈሳዊ ወጣት ማኅበራት በሚቀርቡለት ጥሪዎች መሠረትነት በተለያዩ በዐውደ ምሕረቶችና መድረኮች ላይ የስብከተ ወንጌል አገልግሎቱን በሚገባ ተወጥቷል።

አባቴ የስብከተ ወንጌል አገልግሎቱን ለምእመናን ሲሰጥ ዋነኛ መመሪያው "ሕግህ በልቤ መካከል ነው፤ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ" መዝ. ፴፱፥ ፰ን ተቀብሎ በመደገፍ የተናገረውን መከተል ነበር። እግዚአብሔርን ያስደሰቱትም ብሎ የሚያምኑትንና በተለመደው የማስተማር ጸጋ እንደሚያደርጉት መንፈስ ቅዱስ የገለጠለትን ከመናገርና የእግዚአብሔርን ሕግ ለማስከበር ከመጣር ውጪ ሰውን ለማስደሰት ብሎ የሚያደርገው ነገር አልነበረም።

ምእመናን ለእግዚአብሔር ሕግ እንዲገዙ ከነበረው ከፍተኛ ጉጉትና ዓላማ በመነሣት እምነታቸውን ምሉዕ በሆነ ግንዛቤ ተረድተው እግዚአብሔርን በሃይማኖት ዓይን ለማየት እንዲያስችላቸው ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረትና ክትትል ያደርግ ነበር። ይህንን ሲያደርግም ከማንኛውም የታይታ ኑሮ ርቀው የእግዚአብሔርን ሕግጋትና ትእዛዛት ጠብቀው እንዲኖሩ በማስተማር፣ በመከታተል፣ በማጽናናት፣ በማበረታታት፣ በጸሎትና በጾም በማገዝ፣ በመምከርና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በመገሠጽ ጭምር ነበር፡፡

ከግለሰብ ሕይወት በተጨማሪም ለአገርና ለወገን ለመንግሥትም ይጠቅማሉ ብሎ ያመነባቸውን ትምህርቶች በድፍረትና በግልጽነት ያስተምር ነበር፡፡ ከነዚህ ትምህርቶቹ መካከል የሚከተሉትን ለአማኝነት አቀርባለሁ፡፡

<u>ሀ/ የወታደራዊው መንግሥት መልእክትና የጉዳዩም ጉዞ</u>

ኢትዮጵያን ለአሥራ ሰባት ዓመታት የገዛው ወታደራዊ መንግሥት፣ በዘመኑ መጀመሪያ አካባቢ ከገጠሙት ፈተናዎች አንዱና ዋነኛው

በጉጃም ክፍለ ሀገር ተነስቶ የነበረው የህዝብ አመጽ ነው፡፡ የአመጹ መንስኤ መሬታችንንና መግሬያችንን አይወረስም የሚል ሲሆን፡፡ የወታደራዊውን መንግሥት ሹማምንት አመራርም አንቀበልም የሚል እምቢተኝነት ነበረበት፡፡

ይህን አመጽ በጉልበት ለመቋቋም መሞከት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝን የተገነዘበው መንግሥት፣ ሰላማዊ መፍትሔ ለመስጠት ወሰነ፡፡ ይኸውም ከተለያዩ ጉጃም ንዑሳን ክልሎች የተውጣጡ 'አገሬው ሊሰማቸው ይችላል' ፡' የህዝቡን ሥነ ልቡና ያውቃሉ ተብለው የተመረጡ የክፍለ ሃገሩ ተወላጅ ሽማግሌዎችን መላክ ነበረ፡፡ በዚሁ መሠረት ከተመረጡት የጉጃም ተወላጆች መካከል አባቴ አንዱ ነበረ፡፡

ሽማግሌዎቹ ከጉዟቸው ቀደም ብሎ በቤተ መንግሥት ገለጻና መመሪያ ተሰጥቷቸው ነበረ፡፡ የገለጻውና የመመሪያው ዋንኛ ጭብጥ መንግሥት የህዝብን መብትና ጥቅም ለመጠበቅ ዝግጁ መሆኑን ለህዝቡ ማስረዳትና ህዝቡም ተረጋግቶና ጊዜ ሰጥቶ ራሱን የለውጡ ተጠቃሚ እንዲያደርግ መምከር ነበረ፡፡

አባቴ ይህ ተልዕኮ ሲሰጠው በመጀመሪያ "እኔ ለዚህ ተልዕኮ አልመጥንም፡፡ ሌላ ሰው ብትልኩ ይሻላል፡፡"በማለት ራሱን ለማግለል ሞክሮ ነበረ፡፡ ይሁንንም ያደረገው እንዲያደርስ የተሰጠው መልእክት ተፈጻሚ ስለመሆኑ ግን እርግጠኛ አልነበረም፡፡ ነገርግን "ህዝቡ እኛ ከምንነግረው እናንተ የምትነግሩትን ያምናል፡፡ ይሰማል፡፡ በህዝቡና በመንግሥት መካከል ሊፈጠር የሚችለውን ግጭት ለማስቀረት ከእናንተ የተሻለ ሽማግሌ አናገኝም ስለተባለና በህዝብ ላይ አደጋ እንዲደርስ የማይፈልግም ስለነበረ መልእክቱን ለማድረስ ሄደ፡፡ ህዝቡ እንዲሰበሰብ እየተደረገ በተዘጋጁ መድረኮች ላይ ያደረጋቸው ንግግሮች ሲጠቃለሉ የሚከተለው መልእክት ነበራቸው፡፡

"...መንግሥት መብታችሁንና ጥቅማችሁን ለማክበርና ለማስከበር ፈቃደኛነት ያለው መሆኑን እንድናረጋግጥላችሁ ነው የላከን፡፡ ይ[illegible] የመንግሥት ቃል እውነት ወይም ሀሰት ስለመሆኑ ማረጋገጫ[illegible]

የሚገኘው ወደ ፊት በተግባር በሚገለጡ አሠራሮች ይሆናል፡፡ እኛ መልእክት ለማድረስ ነው የመጣነው፡፡ በተገባው ቃል መሠረት መፈጸሙን መከታተል ደግሞ የእናንተ ፋንታ ነው፡፡ መብታችሁን፣ ክብራችሁንና ጥቅማችሁን የሚጠብቅ ከሆነ ከመንግሥት ምንም የማያጣላችሁ ነገር እንደሌለ እምናለሁ፡፡ የአገሬ የጐጃም ህዝብ! ርስትህን፣ ሃይማኖትህንና ክብርህን ወዳድ እንደሆንክ አውቃለሁ፡፡ የነፍስ ወከፍ መሣሪያህም መብትና ክብርህን የሚደፍር ሲመጣ ለመከላከያ የምትይዘው እንጂ ሌላ ክፉ ሀሳብ የሌለበት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ መንግሥትም የህዝብን መብትና ክብር እጠብቃለሁ አከብራለሁ ሲል ርስትህን ሃይማኖትህንና ክብርህን ማለትም እነዚህን ሁሉ የምታስከብርበትን መሣሪያህን ጭምር ሳይነካ ቃሉን ይጠብቃል ማለት ነው፡፡ መንግሥት ቃሉን እንደሚያከብር አምናለሁ፡፡ እናንተም የተገባላችሁ ቃል ከተከበረ ሌላ የምትሹት ነገር ይኖራል ብዬ አለጠረጥርም፡፡ ከተገባላችሁ ቃል ውጪ ሆኖ በርስታችሁ፣ በሃይማኖታችሁና በክብራችሁ ላይ ለሚመጣ ነገር ግን ወሳኝ እናንተው ራሳችሁ ናችሁ፡፡..." በማለት አስተማረ፡፡

የአገር ሽማግሌዎቹ በተዘዋወሩበት ቦታ ሁሉ የሚሠሩትንና የሚናገሩትን እንዲቆጣጠሩ የተላኩ የፖለቲካ ሹማምንት አብረው የነበሩ ቢሆንም በአባቴ እንደበትና እንቅስቃሴ ማዘዝ አልቻሉም፡፡

ከጉዞ መልስ ስለሁኔታው በደረሳቸው ዘገባ የተበሳጩት የደርጉ ሊቀመንበር ኰሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምና ምክትላቸው ኰሎኔል አጥናፉ አባተ አባቴን ወደ ቤተ መንግሥት አስጠሩት፡፡

"ህዝብ እንዲያረጋጉ ቢላኩ እንዴት የባሰ ጦርነት ቀስቅሰው ይመጣሉ?" ኰሎኔል አጥናፉ ጠየቁት፡፡

"የምን ጦርነት? እኛ ከተመለስን የተነሳ ጦርነት አለ እንዴ?" በማለት ጠየቀ አባቴ፡፡

"ምን ሲያስተምሩና ሲናገሩ ሰምተው እንደመጡ ጠይቅሻለሁ፡፡" ኰሎኔል መንግሥቱ ነበሩ፡፡ ንዴት እየተናነቃቸው ተናገሩ፡፡

"እኔ ቅድሙንም አትምጡኝ ስላልኳችሁ መልእክት አልመጣንም ብዬአለሁ፡፡ ሆኖም ግን ከላኳችሁ ውጪ የተናገርኩት ነገር የለም፡፡ 'ህዝቡን የምታውቁት እናንተ ናችሁ፡፡ ህዝቡን አረጋግታችሁ ኑ አሳችሁን፡፡' ህዝቡ ከርሃቡ ከሃይማኖቱና ከክብሩ ሌላ የሚፈልገው ነገር የለም፡፡ 'መንግሥት እንዚህን አይነካብህም አርጋ ብዬ አስተማርኩኝ፡፡ መንግሥት ይመጣል መንግሥት ይሄዳል፡፡ ቋሚነቱና ዋናው ህዝብ ነው፡፡ ህዝብን መዋሸት አያዋጣም፡፡ እና ሌላ ምን እንዳስተምር ትጠብቁ ነበር? " የሚል መልስ ሰጣቸው፡፡

ኰሎኔል መንግሥቱ በአባቴ መልስ ከመናደዳቸው የተነሳ ከፊታቸው የነበረውን ጠረጴዛ በሽጉጣቸው ሰደፍ ነረቱት፡፡ " አውር ገደል ታስገኛለህ እንጂ አንተንስ ..." ብለው ሊናገሩ ያሰቡትን ሳይጨርሱት ተዉት፡፡ ከቢሯቸው ብዙም ባልራቀ ክፍል ውስጥ ከመሪው ጋር እንዲቆይ ተደረገ፡፡ ከተወሰኑ ሰዓታት በኋላ ወደ ቤቱ እንዲሄድ ተፈቀደለት፡፡

ሰ/ ሐውልቱና የታኅሣሥ ገብርኤል በዓል

ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ. ም. ዓመታዊው የቅዱስ ገብርኤል ንግሥ ሲከበር አባቴ የማስተማር አገልግሎት የሰጠው በብሥራተ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ነበረ፡፡ በዚያ ሊገኝ የቻለውም የአጥቢያው የሰበካ ጉባኤ ባቀረበለት ጥሪ መሠረት ነበር፡፡ ሥርዓተ ቅዳሴውና የታቦቱ ሕት ዑደት ከተከናወነ በኋላ ማስተማር ጀመረ፡፡

"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ አሜን፡፡" ብሎ ካማተበ በኋላ በብዙ ዐውደ ምሕረቶች ላይ እንደሚያደርገው ሁሉ እርሱን ወደ መድረክ ስለጋበዙ ንግግር ያደረጉት አባት ስለ እርሱ ሊቅነት በስፋት ያደረጉትን መግቢያ ንግግር በማስመልከት እርሱ ሊቅ አለመሆኑንና እንደዚያ ያለ ሙገሳ እንደማይገባው በመጥቀስ እጅግ ከፍተኛ ትሕትና በተመላባቸው ቃላትና በተሰበረ አንደበት ተናገረ፡፡



ከዚያም መጽሐፈ ዳንኤልን በመመርኰዝ ንጉሥ ናቡከደነፆር የተባለው የፋርስ ንጉሥ በራሱ መልክ ላሠራው ምስል እንዲሰግዱ ሲጠየቁ አንሰግድም በማለታቸው ወደ እቶን እሳት የተጣሉት ሠለስቱ ደቂቅ ምን ያህል በእግዚአብሔር ይታመኑ እንደ ነበረና የታመኑበት አምላክ እግዚአብሔርም እንዴት ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ ከተጣሉበት እሳት እንደአዳናቸው በመጥቀስ ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጠ፡፡

በመቀጠልም የጊዜው መንግሥት በአንድ በኩል አምልኮተ እግዚአብሔርን ለማጥፋት እየሠራ በሌላ በኩል ደግሞ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አጠገብ የቀይ ኮከብ ምልክት ያለበት ሐውልት ማቆሙ በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንታ ለኖረችው ኢትዮጵያ ትልቅ ስድብና አስጸያፊ የታሪክ ጠባሳ መሆኑን፤ ሕዝቡ ስለሐውልቱ ያለውን ክብር በተለያየ መንገድ እንዲያሳይ ማበረታታቱም ደግሞ ናቡከደነፆር ካሠራው ተግባር የማይተናነስ ድፍረት መሆኑን፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ምእመናንም ክብርን ለእግዚአብሔር እንጂ አምባገነኖች ላቆሙት ሐውልት መስጠት እንደማይገባቸው በመግለጽ ምንም ዓይነት ግፊት ቢደርስባቸው እንደ ሠለስቱ ደቂቅ በእምነታቸው ጸንተው መቆም እንደሚገባቸው በመግለጽ አስተማረ፡፡

ሐ/ ኡ! ኡ! የጎበዝ ያለህ!

በወታደራዊው መንግሥት ዘመን አባቴ በተደጋጋሚ ካስተማረባቸው ቦታዎች አንዱ የጎፋ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ የነበረው መንግሥት በህዝብ ላይ እያደረሰ የነበረው ጭንቅና መከራ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመቀነስ ፋንታ እየጨመረ መምጣቱና ህዝቡን የሚታደግ ተስፋ ጠፍቶ የተማረውም ያልተማረውም፣ ጉበዙም ደካማውም፣ በጽኑ አገዛዝ እየተሰቃየ የነበረበት ወቅት ነበረ፡፡ የአገዛዙ አስከፊነት የፈጠራቸው ምሬቶች የአገሪቱንና የህዝቡን መጻኢ ዕድል ወደ ከፋ ደረጃ ያደርሰዋል የሚል ሥጋት ነበረበት፡፡ በዚህ ሥጋትና ሃሳብ ውስጥ እያለ የግንቦት ስምንት መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተደረገ፡፡ ከዚያ በመነሳት ዘወትር እንደሚያደርገው ሁሉ የዕለቱን ክብረ በዓል በተመለከተ

ሃይማኖታዊ ትምህርት ከሰጠ በኋላ ወደ ሕብረተሰቡና ወደ አገር ችግር በመዞር የሚከተለውን ተናገረ፡፡

"አንድ ዓይነ ሥዉር ይኖር በነበረበት አንድ አገር ከዕለታት በአንዱ ቀን ኡ!ኡ ! ተባለ፡፡ ዓይነ ሥዉሩም ጩኸቱ ወደ መጣበት አቅጣጫ በደንብ አንቅቶ ሲያዳምጥ ኡ!ኡ !የሰው ያለህ! እየተባለ ሲጮኽ ሰማ፡፡ በዚህን ጊዜ ልብሴን አቅርቡልኝ፣ ከዘራዬንም ስጡኝ ብሎ መሪውን ጠርቶ ውሰደኝ ሲል ሚስቱ ሰማች፡፡ ሚስቱም፣

"እርስዎ ደካማ ዓይነ ሥዉር ነዎት ወዴት ሊሄዱ ነው? ምንስ ሊያደርጉ ነው? ይልቅ አርፈው ይቀመጡ፡፡" አለችው፡፡ ዓይነ ሥዉሩም፣

"አገሬ እኮ የሰው ያለህ እያለች ነው፡፡ ምኝ ነሽ እንዴ? እሄዳለሁ!" ብሎ ብዙ ርቀት ከሄደ በኋላ እንደ ገና "ኡ! ኡ! የጉበዝ ያለህ! "እየተባለ ሲጮህ ሰማ፡፡ በዚህ ጊዜ "አሁን 'ለይቷል በል መልሰኝ" ብሎ ተመለሰ ይባላል፡፡ " በማለት አገርንና ወገንንለመመከት የሚችል ጥቂትም ቢሆን አቅም ያላቸው ሁሉ የጉልበታቸውን ማነስና መብዛት ከግምት ሳያስገቡ ለጥሪው ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው በምሳሌ አስተምሯል፡፡

## መ/ መስቀል ኃይላችን ነው!

ወታደራዊው መንግሥት ይፋ መግለጫ ሳያወጣ ወይም አዋጅ ሳያውጅ በውስጠ ታዋቂ ከከለከላቸው ነገሮች አንዱ አምልኮተ እግዚአብሔር ነበር፡፡ በየፖለቲካ ጥናት ክበባትና በጎትመት መልክ በሚሰራጩ የኮሚኒዝም ትምህርቶች አማካይነት "ሃይማኖት የሰዎችን አእምሮ የሚያደነዝዝ ዕፅ ነው፡፡" እየተባለ ከመሰበኩም በላይ በየመሥሪያ ቤቱ የሃይማኖተኛነት አዝማሚያ የሚያሳዩ ሁሉ ንቃተ ሕሊናችሁ ዝቅተኛ ነው እየተባሉ በካድሬዎች ቁጥጥር ይደረግባቸው ነበረ፡፡ በሰንበትና በበዓላት ቀንም ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ አስፈሪ ከመሆኑ የተነሣ ብዙ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመሄድ ታቅቦ ነበረ፡፡ ታላላቅ በዓላትን ለማክበር ወደ ዐደባባይ ይወጣ የነበረው ሕዝብም ብዛት አልነበረውም፡፡ የሚወጣውም በፍርኃት የተሸበበ ነበረ፡፡



በመንግሥት ኃላፊነት ላይ የነበሩ ሰዎች የወለዷቸውን ልጆች በሀርባና በሰማኒያ ቀን ክርስትና ለማስነሣት እየፈሩ ከአዲስ አበባ ውጪ ወዳሉ አብያተ ክርስቲያን በድብቅ እስከ መላክ ድረስ የደረሱበት ሁኔታም ነበረ፡፡ በእንዲህ ያለ ሁኔታ ውስጥ የነበረው ሕዝብ እንደ መስቀልና ጥምቀት በመሳሰሉ ታላላቅ በዓላት ላይ ለመገኘት ሥጋትና ጭንቀት ስለ ነበረበት በመስቀል ዐደባባይም ሆነ በየጥምቀተ ባሕሩ የሚከናወነው ሥርዓት እንደ ወትሮው ደማቅ አልነበረም፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ የቤተ ክህነቱ ባለ ሥልጣኖች አጋጣሚውን እየተጠቀሙ መንግሥት ያሚያራምደውን የአገዛዝ ሥርዓት ማወደሻና መቀደሻ ከማድረጋቸው በተረፈ ከነሱ የሚጠብቀውን የአርአያነት ጠንካራ ሰብእና ማግኘት ሳይቻል ቀረ፡፡በዚህ ምክንያት ሕዝቡ ቃለ ምዕዳናቸውንም ሆነ ጸሎተ ቡራኬያቸውን የሚያዳምጠው በተሰላቸ ስሜትና በኀዘን ነበር፡፡ ደርግም ሕዝቡን በየዐደባባዩና በየአዳራሹ እየሰበሰበ "አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት" እያለ ግራ እጁን እያነሣ እንዲጮህ ያስገድደው ነበረ፡፡

በዚሁ ዘመን ከተከበሩ የመስቀል ደመራ በዓላት በአንዱ ላይ ተገኝተው የነበሩት ክቡር ፕሮፌሰር ነቢያት ተፈሪ በወቅቱ አባቴ ሕዝቡን እንዴት ያስተምር እንደነበረ በማስታወስ ለአሜሪካ ሬዲዮ የአማርኛ ክፍለ ጊዜ እንዲህ በማለት የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡

"በደርግ ዘመን መስቀል በዓል በሚከበርበት ጊዜ አብዮት አደባባይ ይባል ነበረ፡፡ አሁን እንኳ ለስሙ መስቀል አደባባይ ተብሏል፡፡ ለደመራ ወጥተው በሚያስተምሩ ጊዜ ሃያና ሰላሳ ሺህ ሰው ተሰብስቧል፡፡ ትንሽ ይለኛል ብቻ ባልሳሳት አብዮተኛ ፓርቲዎች ወይንም ድርጅቶች አንድ የሆኑበት ጊዜ ነበረና በዚያን ጊዜ ደርግ ሕዝቡን እየሰበሰበ በየአደባባዩ መፈክር ያስተምር ነበረ፡፡ ሁሉም ሰው "አብዮታዊ እናት አገር ወይም ሞት!"እያለ ግራ እጁን እየወረወረ ሁላችንም ብንል ነበረ፡፡ እሳቸው ስለ መስቀል አስተማሩና ከጨረሱ በኋላ አሁን እንግዲህ ይህንን ከተረዳችሁ አሉና መስቀል ኃይላችን ነው! መስቀል መድኃኒታችን ነው!ብለው ቀኝ እጃቸውን አንስተው ይጮሃሉ፡፡ ሕዝቡ ዝም አለ መሰለኝ ኋላ ሁለተኛ ደገሙት፡፡ ሕዝቡ ምን እንደሚፈልጉ ገባው፡፡ ከዚያ ሕዝቡ "መስቀል ኃይላችን ነው! መስቀል

"መድኃኒታችን ነው" እያለ መፈክር አሰማ፡፡ ከዚያ "መድኃኔዓለም ጋሻችን ነው፤ መስቀል መድኃኒታችን ነው"ብሎ ቤቱ አለቀ፡፡ ሕዝቡን ሙሉ በሙሉ ቀየሩት፡፡ ከዚያ ሕዝቡ ተበረታቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ማምራት ጀመረ፡፡ እስከዚያ ድረስ ግን የሃይማኖት ጉዳይ ተዳፍኖ ነበረ፡፡" በማለት ስለሁኔታው የሚያስታውሱትን ተናግረዋል፡፡

## መ/ የንስሐ ጥሪ በአራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን

ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም.የሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል ሲከበር አባቴ በአራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንአስተምረዋል፡፡ ወቅቱ በመላ አገሪቱ ያንዣበበው የርስ በርስ ጦርነት ያየለበት ጊዜ ነበር፡፡ ወታደራዊውን መንግሥት ሳይቀር ፍርሀቱ እስታውቀበት ነበር፡፡ሲሰራ የኖረውን ግፍና በደል ረስቶ የሕዝቡን ድጋፍ ለማግኘት ከፍ ዝቅ ሲል ታይቷል፡፡ ሲያንቋሽሻቸውና ሙልጭ አድርጎ ሲሰድባቸው የነበሩትን ታላላቅ የኢትዮጵያ ነገሥታት በቴሌቪዥን መስኮት ብዙ ጊዜ ያሳያቸው ጀመር ስማቸውንና ዝናቸውን የጦርነት መቀስቀሻና የኃይል መጎተቻ ማድረጉን ልብ ብለናል፡፡ ሕዝቡም በተጠራበት ስብሰባና ሰልፍ ላይ እየተገኘ ይህንኑ የመንግሥትን ቅስቀሳ እንደ በቀቀን እየተቀበለ ለማስተጋባት ተገዷል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነበር የሚያዝያ ጊዮርጊስ የተከበረው፡፡ሥርዓተ ቅዳሴና ውዳሴ ካለቀ በኋላ አባቴ እንዲያስተምር ተራው ተሰጠው፡፡ ስለ ቅዱስ ጊዮርጊስ ክርስቲያናዊ ተጋድሎና በመጨረሻ ስለተቀበለው የሰማዕትነት ክብር በሰፊው አስተማረ፡፡ በትምህርቱ ማጠቃለያ ላይም ዘወትር እንደሚያደርገው በአገርና በሕዝብ ዕለታዊ ጉዳዮች ላይ አተኮረ፡፡

በሕዝብ መገናኛዎችና ስብሰባዎች ላይ በሚደረጉ የጦርነት ቅስቀሳዎች ላይ ትኩረት በመስጠት የሚሰማውን ተናገረ፡፡"የቴዎድሮስ ነኝ፣ የዮሐንስ ነኝ፣ የምኒልክ ነኝ" እያሉ ጉራ መንዛት የማያዋጣ መሆኑን፣ ስማቸው የተጠቀሰው ነገሥታት ዛሬ የሚወዳቸውን ታላቁ የሠራዊት እግዚአብሔርን ጋሻና መከታ አድርገው መሆኑንና በጊዜአቸው ለአገርና ለወገን መሥራት የሚገባቸውን ሠርተው ማለፋቸውን በመጥቀስ ሕዝቡም ሆነ መንግሥት በጊዜአቸው ሠርተው ያለፉትን መሪዎች



ለመተስተብ ከመሞከር ይልቅ የእነርሱን ፈለግ ተከትሎ የራሱን ጋላፊነት ለመወጣት ቢሞክር እንደሚሻል አስተማረ፡፡

አባቴ በዚህ ዕለት ትምህርቱ ላይ፤ በድለውናል፤ ጨቁነውናል ተብለው ሲንቋሸሹ፣ ሲሰደቡ የነበሩ ነገሥታት አሁን ጭንቅ ሲመጣ ስማቸው የጦርነት ኑጋሪት መጉሸሚያ መሆን እንደሌለበት ገልጧል፡፡ በ፲፯ቱ የወታደራዊው መንግሥት ዘመናት ብዙ በደል መሠራቱን፣ የእግዚአብሔር ስሙ መካዱን፣ ዘወትር የክርስቶስ ሙሽራ የሆነችዋ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን "እርጌዋ ቤተ ክርስቲያን ትውደም" ተብላ መረገሟን፣ ከሕዝቡ እጅግ የሚበዛው የኮሚኒዝም ሥርዓት አራማጅ በመሆን ብዛት ባላቸው የዐመጻ ተግባራት መሳተፉን፣ አዕይንተ እግዚአብሔር የተባሉ ካህናት ከግፈኞቹ ጋር በመተባበር እውነትን ችላ ማለታቸውን፣ የሚፈጸመውን ግፍ ዓይተው እንዳላዩ፣ ሰምተውም እንዳልሰሙ መሆናቸውን፣ በዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን በራሷ ካህናት መዋረዷን በዝርዝር አውስቷል፡፡ በትምህርቱ መደምደሚያ ላይም በዚህ ሁሉ የነውርና የበደል ግጥ ውስጥ የተዘፈቁ ሁሉ ተጸጽተው በመመለስ ራሳቸውን በንስሐ ካላነጹ በስተቀር "የቴዎድሮስ ነኝ ፣ የዮሐንስ ነኝ" ማለቱ የትም እንደማያደርስ በመግለጥ አስተምሯል፡፡

## ሬ/ የአዋጅ ምሕላ ጥሪና በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን

አባቴ ለስብከተ ወንጌል በሚሰለፍበት ሁሉ እየተገኙ የጠዋቱን ለማታ፣ የማታውን ለጠዋት ከስ የሚያቀርቡ የውስጥና የውጪ ወሬ አቀባዮችነበሩ፡፡እነዚህ ሰዎች የሚያዚያ ጊዮርጊሱን ትምህርት በምን መልክ ለመንግሥት ደኅንነት ክፍል እንዳቀረቡ በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም በጥቂት ሳምንታት ውስጥ በአገሪቱ ያሉ የሃይማኖት ተቋማት በሞላ ተከታይ ምእመናኖቻቸውን ይዘው የምሕላ ጸሎት እንዲያደርጉ መንግሥት መፈለጉን የሚያሳዩ ምልክቶች መታየት ጀመሩ፡፡በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያን በመገኘት የምህላ ጸሎት እንዲያደረጉ ተቆረጠ፡፡ የመንግሥት ተወካዮችና የቤተ ክህነት ከፍተኛ ባለ ሥልጣናት በተገኙበት ደግሞ የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ይፋ የምህላ ጸሎት እንዲካሄድ ከመንግሥት በቀረበው ጥያቄ መሠረት

ሁሉም ከያለበት ለጸሎት ተሰባሰበ፡፡ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና የቤተ ክህነት ባለ ሥልጣናት በብዛት ተገኝተው ነበር፡፡ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት አባቴ እንዲያስተምር ስለ ስለጠየቁ ወደ ማስተማሪያ ስፍራው በመቅረብ በሕዝቡ ፊት ቆሞ አስተማረ፡፡

በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የተከናወነው የምህላ ፀሎት በተከናወነበት ወቅት ውጥረት የተሞላ ነበረ፡፡ የሥልጣን መንበሩ እየከዳው በነበረው መንግሥትና በጊዜው ዐማጽያን ይባሉ በነበሩት ተቃዋሚዎች መካከል እየተካሄደ የነበረው ጦርነት ወደ መጨረሻዋ የፍልሚያ ሜዳ ወደ አዲስ አበባ ተቃርቧል፡፡ የከተማዋ ፍሬም መጪዎቹ ቀናት ብዙ ጥፋት ሊያስከትሉ ይችላሉ ብሎ ሥጋት ውስጥ ገብቷል፡፡ አባቴ በዚህ ዕለት ያስተማረው ትምህርት መሠረት ያደረገው በትንቢተ ዮናስ ውስጥ የተመዘገበውን የነነዌን ሕዝብ የንስሐ ታሪክ ነው፡፡ ታሪኩን በዝርዝር ካቀረበ በኋላ ባስተላለፈው ትምህርት በዚያ አስጨናቂና አስፈሪ ሁኔታ ውስጥ የወደቀው የአዲስ አበባ ሕዝብ የእግዚአብሔርን እርዳታ ፈልጎ ለምህላ መሰብሰቡ መልካም ሆኖ ሳለ መርሐ ግብሩን ያሰያዙት የሕዝቡ መሪዎች ግን በቦታው አለመገኘታቸው አግባብ አለመሆኑን ተናግሯል፡፡ በቀደሙት የአብዮት ዓመታት መንግሥትም ሕዝብም አብረው ተባብረው እግዚአብሔርን የበደሉ እንደ መሆናቸው መጠን ልክ እንደ ነነዌ ሰዎች መሪና ተመሪ፥ አለቃና ጭፍራ ተብለው ሳይለያዩ በአንድነት በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ መግባት ይገባቸዋል ካለ በኋላ የወቅቱ መሪዎች በዚያ ሰዓትና ቅጽበት ወዴት እንዳሉ በመጠየቅ በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን እንዲያዋርዱና ንስሐ እንዲገቡ ጠይቋል፡፡

በወታደራዊው መንግሥት ዘመን ምእመናን እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል የተጠሙበት ወቅት ስለነበረ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የአባቴን ትምህርት ለመስማት በየሄደበት ሁሉ ይከተሉት ነበር፡፡ ከአንደበተ ርቱዕነቱና ከጥልቅ ዕውቀቱ ባሻገር ለማስተማር መነሻ የሚያደርገውን ርእስ ከአገራዊ ማኅበረሰባዊና ግለሰባዊ ሕይወት ጋር በማዛመድ የሚሰጣቸው ጥልቅ ትንታኔዎች፥ ምክሮችና ተግሣጾች የክርስቲያኖችን ሕይወት ትርጕም ባለው ሁኔታ የሚያንጹ ነበሩ፡፡



በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተፈጸሙ ወቅታዊ ሁኔታዎችን ከምእመናን ሃይማኖታዊ ሕይወትና ብሔራዊ ኃላፊነት አንጻር አጣምሮ የሚያቀርብበት የእርሱ ብቻ የሆነው ተለጥዎና መንፈሳዊ ጸጋም የብዙዎችን ሕይወት ለውጧል፡፡ አባቴ በአንድ ክብረ በዓል ላይ ከተገኘና "የዕለቱን ትምህርት የሚሰጡን አለቃ አያሌው ታምሩ ናቸው፡፡" የሚል መግለጫ ከዐውደ ምሕረቱ ከተነገረ ሕዝቡ በደስታ ይሞላል፡፡ የቆመው ይቀመጣል፡፡ የተቀመጠው ተደላድሎ የትምህርቱን መጀመር በጉጉት ይጠባበቃል፡፡ ከዚያም ትምህርቱን በአንክሮ ይከታተላል፡፡

ስለ አባቴን የሰብከተ ወንጌል አገልግሎት ሁኔታ ኤርምያስ ጉልላት የተባለ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ለታሪክ ትምህርት ክፍል ባቀረበው የ፳፻፪ ዓ.ም.የመጀመሪያ ዲግሪ የመመረቂያ ጽሑፉ ላይ እንደሚከተለው ገልጦታል፡፡

"አለቃ አያሌው ታምሩ ዘዲማ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ምእመናን የሚታወቁት በዓውደ ምሕረት ሲሰብኩ ነበር፡፡ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን በዓላት ሲከበሩ ጳጳሳት ሊባርኩና የበዓሉም ተሳታፊ ሊሆኑ ይመጡና የስብከቱ ድምፅ ማጉያ የሚሰጠው ግን ለሊቀ ሊቃውንት አለቃ አያሌው ታምሩ እንደ ነበረ የሚታወስ ነው፡፡"

በዚሁ የመመረቂያ ጥናታዊ ጽሑፍ ላይየአባቴ አንደበተ ርቱዕነት፥ ልዩ የሰብከተ ወንጌል ችሎታና የቃላቱን ኪነ ጥበባዊ አገላለጽ ጭምር ተወስቷል፡፡

በተጨማሪም"አለቃ አያሌው እንደ ብዙዎች ሰባክያን ሲሰብኩ አያስለቅሱም፡፡ ከሚናገሩበት ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሥነ ቃላዊ ትውፊት ዐብረው ከስብከታቸው ጋር ያዛምዷቸዋል፡፡ ትምህርታቸውን ኢትዮጵያዊ ወግ ያላብሱታል፡፡ ... ሊቀ ሊቃውንት አያሌውን የተለዩ ሰባኪ ሐዋርያ የሚያደርጋቸው መንግሥትንም ቤተ ክህነትንም ትውልድንም ሳይገሥጹ አለማለፋቸው ነው፡፡ " እያለ ይቀጥላል፡፡

በወታደራዊው መንግሥት ዘመን ለነበረው የፖለቲካ ሥርዓት ታማኝነት የነበራቸውና ሌሎችም በወሬና በአሉባልታ ጊዜአቸውን ይፈጁ የነበሩ ሰዎች አባቴን ቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ ኃላፊዎችና ከመንግሥት ባለሥልጣናት ፊት ለመክሰስ የሚቀድማቸው አልነበረም፡፡ በዚህም ምክንያት አባቴ ሰዎች በሚያቀርቡበት ክስ የተነሣ በተደጋጋሚ ወደ አገሪቱ የደኅንነት ቢሮ እየተጠራ ይቀርብ ነበረ፡፡ ለአገር ለወገንና ለቤተ ክርስቲያን የነበረውን ጥልቅ ፍቅር፣ ይልቁንም ደግሞ ከማንም ሊሰወር የማይችለውን መንፈሳዊ ስብእናውንና እውነተኛነቱን ይረዱ የነበሩ የሥራ ኃላፊዎች በአብዛኛው በከፍተኛ አክብሮት ይመለከቱት ስለ ነበረ ብዙ ሊጎዱት አልደፈሩትም ነበር፡፡ በደኅንነት ቢሮ ውስጥ ይሠሩ ከነበሩ ኃላፊዎችም ወቀሳ በዘመዶቻቸው ተጽእኖ በአባቴ ላይ መጥፎ ነገር እንዳይፈጸም ከለላ የሚያደርጉለት ብዙዎች ነበሩ፡፡



# ምዕራፍ ፯
# ሃያ የተጋድሎ ዓመታት
# ፲፱፻፷፯ -፲፱፻፹፯